# የኢትዮጵያ ልማታዊ መንግስት- የመረጋጋት ግንባታ ማዕቀፍን መሰረት ያደረገ ቅኝት

**መልሰው ደጀኔ [1]፣ ሎጋን ኮክራን [1፣ 2፣ 3]**

1 Institute for Policy and Development Research, Hawassa University, Ethiopia
2 Carleton University, Canada
3 Centre for Learning on Evaluation and Results, School of Governance, University of the Witwatersrand, South Africa

**አድራሻ**
Logan Cochrane
Email: logan.cochrane@gmail.com

**እጥርጥር**

ኢትዮጲያ ባስመዘገበችው የኢኮኖሚ እድገት እንዲሁም በሰብዓዊ ልማት አመልካቾች ባሳየችው ለውጥ ሙገሳን እየተቸረች ነው። አንዳንዶች የነዚህን ለውጦች መሰረት መንግሥት የሚያራምደው የልማታዊ መንግሥት ርዕዮት እንደሆነ ያምናሉ፤ ሌሎች ደግሞ የዚህ የልማታዊ መንግሥት ርዕዮት እና በኢትዮጲያ ያለው ትግበራ ለየቅል ይሆንባቸዋል። እስከ 2018 ድረስ መንግሥትንና አካሄዱን የሚሞግቱ ሐሳቦች ተቀባይነት አልነበራቸውም፤ አማራጭ እይታዎችንም የሚያስተጋቡ ፖለቲከኞች፣ ምሁራንና ጋዜጠኞች ለእስር ተዳርገዋል። ነገር ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ይህ የመንግሥት አካሄድ ለውጥ እያሳየ ይመስላል፤ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩም በልማታዊ መንግሥት ርዕዮት ላይ ሙግት እንዲደረግበት ጥሪ አቅርቧል። ይህጥናት የኢትዮጲያን ልማታዊ መንግሥት ርዕዮት በመረጋጋት ግንባታ ማዕቀፍ(a building stability framework assessment) መሰረት ይፈትሻል። በዚህም መሰረት ርዕዮቱ ሚዛናዊ የሥልጣን መዋቅሮች የመፍጠር አቅሙን፣ ሁሉን አቀፍ የኢኮኖሚ ልማት ማምጣቱን፣ ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የሚያስችሉ መንገዶች መዘርጋቱን፣ ስኬታማና ሕጋዊ ተቋማት መፍጠሩን፣ እና የፌዴራል መንግሥቱን ደጋፊ የሆነ በትብብር ላይ የተመሰረተ የቀጠና ከባቢ መሩን ይመረምራል። የልማታዊ መንግሥት ሞዴል ስኬታማ የሆነባቸው አውዶች ያሉ ቢሆንም፤ እንደ መንግሥታዊ አስተዳደር አቅጣጫ ለኢትዮጲያ ከዚህ በላይ ጥቅም የማስገኘቱ አቅም ያበቃ ይመስላል። ከልማታዊ መንግሥት ወደ ልማታዊ ዴሞክራሲ የሚደረግ ሽግግር በሥራ ላይ ያለ ይመስላል። መንግሥታዊ ውሳኔዎችና የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ከዚህ ለውጥ ጋር መሳ ለመሳ መሄድ ይኖርባቸዋል።

**ቁልፍ ቃላት**

የመረጋጋት ግንባታ ማዕቀፍ፣ ልማታዊ መንግሥት፣ ኢትዮጲያ፣ያልተመጣጠነ እድገት/ፍትሀዊ ያልሆነ እድገት

## 1 - መግቢያ

"በአፍሪካ ውስጥ የልማታዊ መንግሥት ጉልህ ምሳሌ ከሆኑ ሀገሮች ኢትዮጲያ ዋናዋ ነች" (Clapham, 2018, p. 1151)

"የዓለም መሪዎች በመለስ የተመዘበውን የኢኮኖሚ እድገት ቢያሞግሱም የእድገቱ መሰረት የሆነውን ፅንሰ ሐሳብ ግን አልተቀበሉተም" (de Waal, 2012, p. 148)

> “መለስ በልማታዊ መንግሥት ፅንሰ ሐሳቡ ውስጥ አንኳር የሆኑትን የፖለቲካዊ ስልትና ድርጊቱን አላካተታቸውም፤ ምክንያቱም እነዚህ ከፅንሰ ሐሳቡ ጋር ስለሚቃረኑ ነው። በተግባርም የሚታየው ይኸው በተግባርና በፅንሰ ሐሳብ መካከል ያለው ተቃርኖ ነው” (Lefort, 2013, p. 461)

የኢትዮጲያ ልማታዊ መንግሥት ሞዴል በተለያዩ ምሁራን ጥናት ተደርጎበታል፤ ከእነዚህም ውስጥ Clapham (2018)፣ de Waal (2012)፣ Lefort (2013)፣ እና Abbink (2017) ይገኙበታል። የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ድንገተኛ ኅልፈት ባስከተለው የፖለቲካ ለውጥ ምክንያት በኢትየጲያ ውስጥ ባለው ልማታዊ መንግሥት ላይ ውይይቶች መነሳት ጀምረዋል። ኢትዮጲያ ላይ ትኩረት ያሳደረው የፖለቲካ ለውጡ ብቻ ሳይሆን ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ እድገትም በመታየቱ ነው (World Bank, 2017)፤ እንዲሁም ሀገሪቱ በሚሊኒየሙ የልማት ግቦች በተለይም በጤናውና በትምህርት ዘርፉ ባሰመዘገበችው (UNDP, 2015)አንጻራዊ እድገት ምክንያት ነው። የእነዚህ ለውጦች መሰረት የሆነው ፈላጭ ቆራጭና የተረጋጋ ባሕሪ ያለው የኢትዮጲያ ልማታዊ መንግሥት ሲሆን የረጅም ጊዜ እቅድ በማዘጋጀት፣ የሀብት አጠቃቀምን በማስተካከልና አቅሙን በመገንባት ለውጦቹን እውን አደርጓል። በሌላ ጎን የመንግሥቱ ፖሊሲዎች ከሰብዓዊ መብት ጥሰቶችና ጭቆናዎች ጋር በተገናኘ ጥያቄዎች ይነሱባቸዋል (Amnesty International, 2012; Freedom House, 2018; Human Rights Watch, 2015)። የመንግሥቱን የአስተዳደር መንገድ አስመልክቶ የተለያዩ ትርክቶች አሉ፤ የልዩነቶቹም መሰረት የሚወሰነው በሚጠቀሙበት መረጃ አልያም በሚያተኩሩበት የለውጥ አይነት ላይ ነው።

የኢትዮጲያ መንግሥት የሚከተለው የአሰትዳደር መንገድ የልማታዊ መንግሥት እንደሆነ እራሱ ይናገራል። ጥሩ የሆነ የመንግሥት አስተዳደር መንገድ መፈለግ ወሳኝ እና የጊዜው ጥያቄ ነው፤ ነገር ግን የኢትዮጲያ መንግሥት ይህንን ርዕዮት መከተል ከጀመረ ወዲህ በዚህ ርዕዮት ላይ የሚደረግ ምንም አይነት ብሔራዊ ክርክርና ትችት ተቀባይነት የለውም ነበር (Oakland Institute, 2013)። በ2018 መንግሥት በአስተዳደር መንገዱ ላይ የሚሰነዘሩት ትችቶች ላይ ይዞት የነበረውን የረጅም ጊዜ አቋም የመቀየር አዝማሚያ አሳይቷል። ሰኔ 2018 በመለስ ዜናዊ የአመራር አካዳሚ አዘጋጅነት (ስያሜውን ያገኘው ከቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ነው) ‘‘ልማታዊ መንግሥት እና አመራር’’ በተሰኘ ርዕስ በተደረገ ስብሰባ ወቅት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን በኢትዮጲያ የልማታዊ መንግሥት ሞዴል ላይ የምርምር ሥራዎች እንዲደረጉ ጥሪ አቅርቧል[1]። መንግሥት ሲከተለውና ሲያራምደው የቆየው የልማታዊ መንግሥት ሞዴል ያስገኘውን ጥቅም፣ ያጋጠሙትን ተግዳሮቶችና የወደፊት እድሎች መመርመር ለሀገሪቱ ጥቅም እንዳለው ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ አሳስቧል። ይህም ጽሑፍ ለዚህ ጥሪ ምላሽ ለመስጠት የተዘጋጀ ነው። በተለይም የኢትዮጲያን ልማታዊ መንግሥት ሞዴል በ ‘መረጋጋት ግንባታ ማዕቀፍ’ (DFID, 2016) ይፈትሻል። ይህ ማዕቀፍ አምስት አምዶች አሉት፤ እነዚህም (1) ሚዛናዊ የሥልጣን መዋቅሮች (2) አሳታፊ የኢኮኖሚ ልማት (3) ግጭትን የመፍቻ መንገዶች (4) ስኬታማና ሕጋዊ ተቋማት እና (5) ተባባሪ የቀጠና ከባቢን የመፍጠር አቅም ናቸው።

---

[1] ይህ በመለስ ዜናዊ የአመራር አካዳሚ የተደረገው ስብሰባ በሰኔ29 2018 በኢትዮጲያ ቴሌቪዥን ተላልፏል። ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን ይህንን ጥሪ ያቀረበበትን ንግግሩን ያደረገው በአማርኛ ሲሆን፤ እኛ እስከምናውቀው ድረስ ግን ቴሌቪዥን ጣቢያው የዚህን ስብሰባ ቀረፃዎች በድረ-ገጹይ አላስቀመጠም።

በኢትዮጲያ ልማታዊ መንግሥት ሞዴል ላይ ቀደምት ጥናቶች ተደርገዋል። ጥናቶቹ የሞዴሉን መነሻዎችና ሀገሪቱን ከማሳደግ አንጻር ያለውን አቅም (Clapham, 2018)፣ እንደ መንግሥት አስተዳደር መንገድ ሞዴሉ ያለውን ባሕሪ (Gebremariam & Bayu, 2017)፣ ሞዴሉ ከገበሬው ጋር ያለውን መስተጋብር እና ግንኙነት (Planel, 2014)፣ ከብሔረሰቦች ስብጥር አንጻር ሞዴሉ የሚጫወተውን ሚና (Abbink, 2011)፣ እና የሞዴሉ መሰረት የሆነውን 'አብዮታዊ' ጽንሰ ሐሳብና ከዚህም ጋር ተያይዞ ያለውን የሀገር ግንባታ (Vaughan, 2011) መርምረዋል። Routely (2012, p. 3) ልማታዊ መንግሥት 'ማሕበራዊ ፍትሕ' እና/ወይም 'ኢኮኖሚያዊ ብልጽግና' ለማስገኘት አይነተኛው መንገድ እንደሆነ ትሞግታለች። በኢትዮጲያ ያለው ልማታዊ መንግሥትም ባለፈው አሥር ዓመት የሁለት አሐዝ የማክሮ ኢኮኖሚ እድገት አሰመዝግቧል (2005/2006–2015/2016) (World Bank, 2017; Cochrane & Bekele, 2018)፤ ይህም ጽሑፍ የልማታዊ መንግሥት ሞዴል አሳታፊ ልማት ከማምጣት አንጻር ያለውን አቅም ይፈትሻል። ይህንን ምርምር ስናደርግ በ2018 አዲስ ጠቅላይ ሚኒስትር ወደ ሥልጣን ከመምጣቱ ጋር ተያያዞ ያለውን ለውጥ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባትና ከቀደምት ዓመታት ይህ ለውጥ ያመጣውን ልዩነት በማነጻጸር ይሆናል።

## 2 - የኢትዮጲያ ልማታዊ መንግሥት

የኢትዮጲያ መንግሥት የልማታዊ መንግሥት ቅርጽ አለው፤ መገለጫዎቹም፡- ራዕይ ተኮር የሆነ፣ ጠንካራ እና ጣልቃ ገብነት ያለው፣ ለሰው ሐብት ልማት ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጥ እና፣ በዕቅድ ዝግጅትና በማስተባበር መጠነኛ ስኬት ያለው ናቸው (Woldegiyorgis, 2014)። Clapham (2018) ኢትዮጲያ በአፍሪካ ውስጥ የልማታዊ መንግሥት አይነተኛ ማሳያ እንደሆነች ይናገራል። እንደ Zenawi (2012) አገላለጽ ደግሞ በኢትዮጲያ የሚታየው ልማታዊ መንግሥት ያለ ሌሎች ተጽዕኖ ራሱን የሚያስተዳድርና እና በሀገር ውስጥም የበላይነቱን ያረጋገጠ (የግራምስኪ መንግሥት መሳይ) ነው። አክሎም ልማታዊ መንግሥታት አስፈላጊ ፖሊሲዎችን በስኬት ለመተግበርና በዘላቂነት ለማስቀጠል አቅም እንዳላቸው፣ ይህንንም ለማድረግ የሚያስችላቸው በምርጫ ኡደቶች ስለማይስተጓጎሉና ተጽዕኖ ሊፈጥሩባቸው ከሚችሉ አካላት ነጻ ስለሆኑ እንደሆነ ያስረዳል።

ሆንግ ኮንግ፣ ሲንጋፖር፣ ደቡብ ኮሪያ እና ታይዋን በልማታዊ መንግሥታትነት በአብነት የሚጠቀሱ ምሳሌዎች ሲሆኑ፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ቻይና፣ ሩዋንዳ፣ ቬይትናም እና ኢትዮጲያ ከእነዚህ ሀገራት ተርታ ይሰለፋሉ (Carothers & de Gramont, 2013)። የእነዚህ ሀገራት ተሞክሮ እንደሚያሳየው የልማታዊ መንግሥት ሞዴል የመንግሥት አመራር የሀገርን ሐብትን በማስተባበር ቀጥተኛ ሚና በመጫወት ትልልቅ ሀገር አቀፍ የልማት ሥራዎችን ለመተግበር እንዲችል ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። ነገር ግን አሳሳቢው ጥያቄ የእነዚህ ጥቅሞች ዘላቂነትና በቀጣይነትም የሚኖራቸው መልክ ነው። እንዲያውም አንዳንድ ማስረጃዎች እንደሚያሳዩት ልማታዊ መንግሥታት የሲቪል ማሕበራትንና የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ድምጽ በማስተናገድ የሥልጣን ሚዛኑን መጠበቅ ካልቻሉ፣ ዴሞክራሲን ከማስፈንና አሳታፊ ከመሆን በተቃራኒ ወደ አምባ ገነንነትና ፈላጭ ቆራጭነት ያመራሉ (Dashwood & Pratt, 1999)። መለስ ዜናዊ ይህንን ይቃወማል፤ ''በኢትዮጲያ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎችና የሲቪል ማሕበራት እውነተኛና አሳታፊ የፖለቲካ ልማድና ዘላቂ ልማት በማምጣት ፈንታ በቀላሉ የጥቅም ተጽእኖ ውስጥ ይወድቃሉ'' ብሎ ይሞግታል (de Waal, 2012, p. 154)።

የኢትዮጲያ መንግሥት ልማታዊ መንግሥት ከመሆኑ የተነሳ ያገኛቸው በርካታ ጥቅሞች አሉ። ለአብነትም፡- የጤና አገልግሎት ሽፋንን ትርጉም ባለው መልኩ ጨምሯል (NPC, 2015, 2017)፣ በሁሉም ደረጃዎች ያለው የትምሕርት ተደራሽነት አድጓል (NPC, 2015)፣ የሀገሪቱ የኢኮኖሚ እድገት በተከታታይ አመታት በዓለማችን ከፍተኛ ከሚባሉት አንዱ ሆኗል (World Bank, 2017)፣ የመንገዶችና የግንኙነት መረብ ዝርጋታዎች እጅጉን ጨምረዋል (NPC, 2017)፣ ውጤታማነታቸው ምንም አከራካሪ ቢሆንም እንኳ ብዙ አዳዲስ የመሰረተ ልማት ፕሮጀክቶች ተጀምረዋል (NPC, 2016)፣ በአፍሪካ በትልቀቱ ሁለተኛ የሆነው የሴፍቲኔት መርሐግብር በሥራ ላይ ነው (Berhane, Gilligan, Hoddinott, Kumar, & Taffesse, 2014)፣ ቀጥተኛ የውጪ ኢንቨስትመንት አሁንም ከፍተኛ እንደሆነ ቀጥሏል (Clapham, 2018)፣ በሚሊኒየሙ የልማት ግቦች ላይ እየተመዘገበ ያለው ለውጥ አበረታች ነው (NPC, 2015)፣ እና በቀጠናው ያለው መረጋጋት ከተለመደው ይልቅ አስተማማኝ ነው (de Waal, 2015)። ነገር ግን እነዚህ ሁሉ ለውጦች ልማቱ ችግር አልባ ለመሆኑ ማረጋገጫዎች አይደሉም።

እነዚህን በከፍተኛ ፖለቲካዊ ግፊት የመጡ ለውጦችን እውን ለማድረግ መንግሥት ብዙ ጫናዎችን አድርጓል። ብዙ ጭቆናዎች፣ አለመቻቻሎችና ግፊቶች ተስተውለዋል፤ እንደ Abbink (2011, 2017) እና Lefort (2013) አገላለጽ እነዚህ ጫናዎች መንግሥት ሥልጣኑን ለማስጠበቅ ባላው ዓላማና ከፍተኛ ቁጥጥርን ከማድረግ የመነጩ ውጤቶች ናቸው። ዓለም አቀፉ ማሕበረሰብም በኢትዮጲያ ውስጥ ያለውን ‘‘እጅግ በጣም አናሳ የዲሞክራሲና የሰብዓዊ መብት ጥበቃ ሂደት’’ ትኩረት እንዳልሰጠው አንጋፋው የ ፖለቲካ ምሁር Christopher Clapham (2018, p. 11) ያስረዳሉ። የሲቪል ማሕበረሰቡ እንቅስቃሴዎች እጅጉን ውስን እንዲሆኑ ተደርጓል (Cochrane & Betel, 2018; Sisay, 2012)። ሚዲያው፣ ጋዜጠኞችና ጦማርያን ከፍተኛ ክትትል ሲደረግባቸው፣ ከዚህ ባለፈ የተቃውሞ ድምጾችን በሚያሰሙት ላይ የሽብርተኝነት እና የሀገር መክዳት ክስ ይመሰረትባቸዋል (Human Rights Watch, 2015)። የመንግሥት መርሐግብሮች ላይ ለመሳተፍ ፈቃደኛ ባልሆኑና ከመንግሥት በተለየ አቅጣጫ የሚሄዱ ግለሰቦች በተለያዩ መንገዶች ምርጫ ላይ መሳተፍ እንዳይችሉ ይደረጋሉ፣ ይገለላሉ፣ ወይም ለእስር ይዳረጋሉ (Cafer, Willis, Shimelis, & Mamo, 2015; Cochrane & Tamiru, 2016; de Waal, 2015)። የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች እንዲመሰረቱ ፍቃድ ቢሰጣቸውም ከፍተኛ ቁጥጥር ይደረግባቸዋል፣ መሪዎቻቸውም ለረጅም ጊዜያት በእስር ይቆያሉ (Abbink, 2017)። ምርጫዎችም የሚደረጉት ለይስሙላ ነው፤ በ2015 የተካሄደውና የገዢው ፓርቲ ጥምረት 100% ያሸነፈበት ምርጫ ለዚህ አስረጂ ነው (Clapham, 2018)።

## 3 - የመረጋጋት ግንባታ ማዕቀፍ

የመረጋጋት ግንባታ ማዕቀፍ የተዘጋጀው ‘‘ወደ ኋላ የሚቀር ማንም ሰው መኖር የለበትም’’ የሚል ግብን ይዘው በተነሱት የዘላቂ የልማት ግቦች እና የ 2030 አጀንዳን በመንተራስ ነው። ልማታዊ መንግሥትን በተመለከተ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን የቀረቡትን ጥያቄዎች ለመመለስ በተሞክሮ የተደገፉ ማስረጃዎችን ማቅረብ ያስፈልጋል። ይህን መሰል ማስረጃም ለማቅረብ የመረጋጋት ግንባታ ማዕቀፍ አይነተኛው መንገድ ነው፤ ለዚህም ብቁ የሚያደርገው ማዕቀፉ ጽንሰ ሐሳብን የሚመረምር አልያም ውሳኔ ሰጪዎች ከሚያጋጥሟቸው ተግዳሮቶች የተፋታ የምርምር መንገድ ሳይሆን ውሳኔ አሰጣጥን ለመደገፍ ተግባራዊ መንገዶችን የሚጠቁም ስልት በመሆኑ ነው። ማዕቀፉ አምስት አምዶች ሲኖሩት እነዚህም አንድ ሀገር፣ ማሕበረሰብ ወይም ክልል እንዲያድግና ግጭቶችንም በሰላማዊ መንገድ መፍታት እንዲችል፣ በአጠቃላይም ልማቱ ዘላቂ

እንዲሆን የሚያስችሉ ምሰሶዎች ናቸው (DFID, 2016, p. 5)። እነዚህም አምዶች (1) ሚዛናዊ የሥልጣን መዋቅሮች (2) አሳታፊ የኢኮኖሚ ልማት (3) ግጭትን የመፍቻ መንገዶች (4) ስኬታማና ሕጋዊ ተቋማት እና (5) ተባባሪ የቀጠና ከባቢን የመፍጠር አቅም ናቸው። በዚህ ጽሑፍም እነዚህን አምዶች በመጠቀም የኢትዮጲያን ልማታዊ መንግሥት እንፈትሻለን። ነገር ግን ይህ ማዕቀፍ ውሱን እና ለሁሉም ዓላማ የማይውል እንደሆነ ታሳቢ ማድረግ ያስፈልጋል፣ የዚህ ማዕቀፍ ውስንነቶችም ከዚህ በታች ይቀርባሉ። በአጠቃላይም ይህ ጽሁፍ የዚህን የመንግሥት የአመራር መንገድ የሚያሰገኘውን ጥቅሞች፣ የሚፈጥረውን ዕድሎች እንዲሁም የአመራር መንገዱ ያሉበትን ውሱንነቶች ከሚፈተሸባቸው ከብዙ አካሄዶች አንዱን በመጠቀም የተጻፈ ሆኖ ሊታይ ይገባዋል።

እንደ መረጋጋት ግንባታ ማዕቀፍ አገላለጽ ሚዛናዊ የሥልጣን መዋቅሮች የአንድን ሀገር መሰረት ለማጠንከር ወሳኝ ሚና የሚጫወቱ ሲሆን እንዲህ ዓይነት የሥልጣን ሚዛናዊነትን ለመፍጠር ማሕበረሰባዊ ተሳትፎን ማሳደግ፣ ግጭቶችን መከላከል፣ እና 'ተጠያቂነትና ግልጽነትን' ማስፈን ይጠይቃል (DFID, 2016)። አሳታፊ የኢኮኖሚ ልማት ስንል ደግሞ አጠቃላይ ማሕበረሰቡ የእለት ተእለት ሕይወቱን በሚመለከቱት ጉዳዮች አጀንዳን ለመቅረጽ እና ውሳኔን ለማስተላለፍ ተሳትፎ እንዲያደርግ ሰፊ ምሕዳር እንዲፈጠርለት መንግሥት የሚፈጥረውን እድል ያሳያል (DFID, 2016)። ይህ አይነቱ አሳታፊነት የተመሪው ድምጽ ፈጽሞ ከማይሰማበት፣ ከላይ ወደ ታች በእዝ ከሚተላለፍበትና ፈላጭ ቆራጭ ከሆነ የመንግሥት አካሄድ ጋር ሲነጻጸር ልዩነቱ ግልጽ ነው። በመረጋጋት ግንባታ ማዕቀፍ መሰረት ሰዎች ግጭቶችን የሚፈቱባቸው መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ መንገዶች በሙሉ ግጭቶችን ለመፍታት ሥራ ላይ ይውላሉ። በተጨማሪም ሰላምን ለማስፈን ሴቶችን ጨምሮ የተለያዩ የማሕበረሰብ ክፍሎች የሚጫወቱትን ሚና ግንዛቤ ውስጥ ያስገባል። መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ስኬታማና ሕጋዊ ተቋማትን መገንባት ማሕበራዊ ፍትሕ እና አሳታፊ ልማት ለማምጣት ቅድመ ሁኔታዎች እንደሆኑም የመረጋጋት ግንባታ ማዕቀፍ ያቀነቅናል። ማሕበራዊ ፍትሕ እና መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን እነዚህ ተቋማት የሚሰጡት አገልግሎት የሕዝቡን ዋስትና የሚያረጋግጥ፣ ኢኮኖሚያዊ መረጋጋትን የሚያሰፍን፣ እኩልነት የተሞላበትና ፍትሐዊ ሊሆን የግድ ነው። አምስተኛውና የመጨረሻው የመረጋጋት ግንባታ ማዕቀፍ አምድ ሰፋ ካለው የቀጠና ከባቢ ጋር ግንኙነት የሚፈጠርበት እና በተለይም ከአጎራባች አካባቢዎች ጋር ዘላቂና ሰላማዊ ግንኙነት የመፍጠር አቅምን ያሳያል። ይህ አምድ በተጨማሪም ማሕበረሰቡ ለጉዳት ተጋላጭ እንዳይሆን ሀገሪቱ እንደ ንግድ ያሉትን ሕይወት-ለዋጭ ተግባራትን የማበረታታት አቅሟንም ያሳያል (DFID, 2016)።

የኢትዮጲያን ልማታዊ መንግሥት ለመፈተሽም እነዚህን የመረጋጋት ግንባታ ማዕቀፍ አምዶች እንጠቀማለን። ይህን አሰሳ ከማድረጋችን በፊት ግን የተወሰኑ ነጥቦች ግልጽ ሊሆኑ ያስፈልጋል። ይህ ማዕቀፍ እያንዳንዱ የመንግሥት ተቋም ባሕሪይና ተቋማዊ መዋቅር ምን መምሰል እንዳለበት በዝርዝር አያስቀምጥም፤ በተጨማሪም የአምዶቹንም ቅደም ተከተል አይወስንም። እንዲህ ዓይነት ዝርዝር ገለጻ አለመኖሩ አስፈላጊ እንደሆነ እናምናለን። የተቋማት ግንባታ፣ የፖሊሲና ሕጋዊ ማዕቀፎች እድገት፣ እንዲሁም አጠቃላይ ማሕበረሰባዊ ለውጥ ወጥነት የሌለው፣ ካለው ነባራዊ ሁኔታ፣ እድልና እክል ጋር የሚለዋወጥ ነው (Ang, 2016)። የዚህም ማዕቀፍ ዓላማ ሰላማዊ፣ አሳታፊ፣ ሚዛናዊ፣ እና ግልጽ ማሕበረሰብን መመስረት ሲሆን በዚህ ሂደት ውስጥ የሚያጋጥሙትን አዳጋች ውሳኔዎች በሚገባ ይረዳል። ነገር ግን ይህ ማዕቀፍ የቀማሪዎቹን መላምት በተለይም በእንግሊዝ የዓለም አቀፍ ልማት ክፍል (DFID) ውስጥ ያሉ ተመራማሪዎችን አስተሳሰብ እንደሚያንጻባርቅ ግልጽ ነው። በዚህም ምክንያት ማዕቀፉ የተሰወኑ ጉድለቶች እንዳሉት ብንረዳም ሀገር-አቀፍ ግምገማዎችን ለማድረግ ሰፊ ማዕቀፍ አለው። በተጨማሪም

ምንም እንኳን የተመራማሪዎቹን አስተሳሰብ ቢያንጸባርቅም የማዕቀፉን አምዶቹ የወለዱት መሰረታዊ መላ-ምቶችና መነሻ ሀሳቦች የተለያዩ ሀገራትን ሁኔታ ለመፈተሽ ሰፊ እይታ አላቸው።

ሀገር ለመባል ብቁ ላልሆኑ መንግሥታት ጥቅም ላይ የሚውልን ማዕቀፍ ለዚህ አሳሳ መጠቀማችን አንባቢን ግር ሊያሰኝ ይችላል። የኢትዮጲያ መንግሥት እንደ ሀገር ለመቆጠር ብቃት የለውም የሚልን ሙግት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ እያቀረብን አይደለም። ነገር ግን እንደ መረጋጋት፣ ሰላምን ማስፈን፣ አሳታፊነት እና ዘላቂ ልማት አይነት ባሕርያት በዚህ መዋቅር የተለየ አትኩሮት ይሰጣቸዋል፤ እነዚህም ባሕርያት ከኢትዮጲያ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ተዛምዶ እንዳላቸው እናምናለን። አሁን በስልጣን ላይ ያለው መንግሥት የተመሰረተው ኢትዮጲያ በጦርነት ውስጥ በወጣች ማግስት ነው፤ እንዲሁም በ1990ዎቹ ውስጥ ብሔርን እና ቋንቋን መሰረት ያደረጉ ብዙ የሀገር ውስጥ ግጭቶችን እና ከ1998 እስከ 2000 ደግሞ ኢትዮጲያ ከኤርትራ ጋር ጦርነት ላይ ነበረች። በቅርቡም ኢትዮጲያ ረዘም ላሉ ጊዜያት በአስቸኳይ ጊዜ አዎጆች ውስጥ ነበረች፤ ለአብነትም ከጥቅምት 2016 እስከ ነሐሴ 2017፣ እንዲሁም በድጋሚ ከየካቲት 2018 እስከ ሰኔ 2018። ከ2016 ጀምሮ በተደረጉት ሕዝባዊ አመጾች ምክንያትም አለመረጋጋቱ አዲስን መልክ ይዟል (Kestler-D'Amours, 2018; BBC News, 2016)። ከፖለቲካዊ ተግዳሮቶቹም በተጨማሪ ሀገሪቱ ላይ በሚከሰተው ድንገተኛ ድርቅ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ሰብዓዊ እርዳታ አስፈልጓቸዋል (ReliefWeb, 2018)። እነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች ኢትዮጲያን ሀገር ለመሆን ብቁ ያልሆነች አያደርጓትም፤ ነገር ግን የመንግሥታት ተዓማኒነት ዝቅተኛ ከሆነባቸውና ዜጎቻቸውም ለጉዳት ተጋላጭነታቸው ከፍተኛ ከሆነባቸው ሀገራት ተርታ እንድትመደብ ያስገድዷታል።

የዚህ ጥናት ቁልፍ ውሱንነት የአሰሳው ማዕቀፍ የተለመደ አይነት መሆኑ ነው። በጊዜና በቦታ ያልተወሰኑ እና ልዩ ምክረ-ሐሳቦች በማዕቀፉ አይሰነዘሩም። ይህ ማዕቀፍ አጠቃላይ ገለጻዎችን ከማድረግ በተጨማሪ ለትግበራዎች የሚጠቅሙ መለኪያዎችንም አያስቀምጥም። በዚህም ምክንያት ማዕቀፉ እንደ መምሪያ የሚያገለግል ሲሆን ከ ግላዊ አመለካከቶች ግን የጸዳ አይደለም። የኢትዮጲያን ልማታዊ መንግሥት ጥቅሞች፣ የሚፈጥራቸውን እድሎች እንዲሁም ያሉበትን ጉድለቶች ለመፈተሽ እያንዳንዱን የማዕቀፉን አምዶች እንደ ገላጭ ምሳሌዎች እንጠቀምባቸዋለን፤ ነገር ግን እነዚህ ምሳሌዎች ብቻ ይህን መንግሥት ሙሉ በሙሉ እንደማይገልጹት እሙን ነው። በእነዚህም ምክንያቶች ይህ ጥናት ይህንን የመንግሥት የአስተዳደር ዘይቤ ለመፈተሽ አንዱ መንገድ እንጂ ብቸኛው አይደለም። ስለሆነም በተለያዩ ዘይቤዎች ይህን መሰል ፍተሻዎች ቢደረጉ መረዳታችንን ይበልጥ ያዳብሩታል።

## 3.1. ሚዛናዊ የሥልጣን መዋቅር

'ሚዛናዊ የሥልጣን መዋቅሮች'ን መፍጠር ለአጭርና ለረጅም ጊዜ ጥቅምን የሚያስገኝና በፖለቲካ ልሂቃን መሐከል ስኬታማና ፍትሐዊ የሥልጣን ክፍፍል የሚፍጥር መንገድ ሲሆን የጾታ ውክልናንም ለማረጋገጥ አይነተኛ መንገድ ነው። ይህን የሥልጣን ክፍፍልም በዘለቄታው ለማስቀጠል ብቁና አሳታፊ የሆኑ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ተቋማት መኖር ወሳኝ ጉዳይ ነው። ይህንንም ለመተግበር ሴቶችን ጨምሮ የተለያዩ የተገለሉ የማሕበረሰብ ክፍሎችን ለማሳተፍ ወሳኝ ፖለቲካዊ ለውጦችን መተግበር ይሻል (DFID, 2016)። በመሆኑም ሚዛናዊና ብቁ የምርጫ ሥርዓት፣ ልዩ ልዩ አመለካከቶች የሚሰተናገዱበት ሰፊ የፖለቲካ ምሕዳር፣ እና አናሳ የማሕበረሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ የሚሆኑበት ኢኮኖሚያዊ መድረክ ሚዛናዊ የሥልጣን መዋቅርን በአግባቡ ይገልጹታል።

ከ 2018 በፊት ኢትዮጲያውያን ውሱን የፖለቲካዊ መድረክ ነበራቸው። በኢትዮጲያ እየጎለመሰ የመጣው ልማታዊ መንግሥት ፍጹም ታዛዥነትን ሲጠይቅ፣ ተቃዋሚ ድምጾችንም ይቀጣ ነበር። ከ 1970ዎቹ ጀምሮ መሰል ጉዳዮችን ሲከታተል የቆየው René Lefort (2013, p. 465) እንደሚያስረዳው ''በልማታዊ መንግሥት ውስጥ ከላይ የሚመጡ ትዕዛዞች ምንም እንኳን አላስፈላጊና ነባራዊ ሁኔታዎችን ያላገናዘቡ ቢኖሩም ከመፈጸም አይስተጓጎሉም''፤ ይህም በትግበራቸው ወቅት እክል እንዲገጥማቸው ከማድረጉም በተጨማሪ አማራጭ ሐሳቦችም ፈጽሞ እንዳይስተናገዱ ይደረጋሉ። የልማታዊ መንግሥት ትርክትም መንግሥት ፈላጭ ቆራጭ እንዲሆን፣ የቁጥጥር አድማሱን እንዲያሰፋና፣ ሥልጣኑም ሥር እንዲሰድ መንገዱን ጠርጎለታል (Abebe, 2014)። 'አብዮታዊ ዲሞክራሲ' በሚሰኘውም የመንግሥት መሪ ፍልስፍና አገላለጽ የገጠሩ አርሶ አደር የዚህ መንግሥት የድጋፍ መሰረት ሲሆን፤ ይህም ሰፊ ሕዝብ የራሱን እጣ ፈንታ ለመወሰን ብቁ ያልሆነና በተቃራኒው 'ያልተማረ'፣ በ'ኪራይ ሰብሳቢዎች' ለመጭበርበር ተጋላጭ የሆነና በዚህም ምክንያት የመንግሥት 'ጥበቃ' እንደሚያሻው ተደርጎ ይቆጠራል (Lefort, 2013)። ነገር ግን ከዚህ እሳቤ በተቃራኒ ጠንካራና ዘላቂ የሆነ መረጋጋት የሚመጣው ብዙኃኑን የማሕበረሰብ ክፍል በፖለቲካው መድረክ ላይ በማሳተፍ እንደሆነ ብዛት ያላቸው ማስረጃዎች ያሳያሉ (DFID, 2016)።

ኢትዮጲያ ፈላጭ ቆራጭ በሆኑ መንግሥታት በመተዳደር ረጅም ዘመናትን አሳልፋለች (Pankhurst, 1966)። በዚህ ረገድ እጅግ ውሱን የሆነ የፖለቲካ ምሕዳር ለሀገሪቱ አዲስ ነገር አይደለም። በቅርቡም እየተስተዋለ ያለው አስተዳደር የእድሜ ጠገቡ ልምምድ ነጸብራቅ ሲሆን መልኩን ቀይሮና የልማታዊ መንግሥትን ካባ ደርቦ ልሂቃን ከላይ ወደ ታች በሚያስተላልፉት እዝ የሚመራ ሆኖ ቀርቧል (Abbink, 2017)። የዚህ እይነት አስተዳደር እሳቤ ቀደምትና ጥልቅ መሰረት ቢኖረውም (Vaughan, 2011) የአስተሳሰቡ መሐንዲስና አቀንቃኝ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ (d. 2012) ነው። ዴሞክራሲ ልማትን ለማፋጠን መሰናክል እንደሚፈጥር መለስ ያስረዳል (Zenawi, n.d.; 2012)፤ ለዚህም እንደ አንድ ማሳያ የሚጠቀመው ለአጭር ጊዜ የሚቆዩትን የምርጫ ዑደቶች እና በዚህም ምክንያት የሚፈጠረውን የፖሊሲና መርሐ-ግብር ትኩረት ለውጦችን ነው። እነዚህን ተግዳሮቶች ለማለፍ ብቸኛው መንገድ ፈላጭ -ቆራጭ የሆነ አስተዳደር እንደሆነ መለስ አያምንም፤ ነገር ግን እንደ ጃፓን እና ስካንዲኔቪያ ላይ ያሉት የረጅም ጊዜ ጥምረቶች ዴሞክራሲን እና ልማትን አብረው ማስኬድ እንደሚያስችሉ ያምናል። ይህ መሰሉ አካሄድ በመለስ ተመራጭ ሲሆን ዘላቂ መረጋጋትን ለማስፈን ሰፊው የገጠር ሕብረተሰብ እምቅ ኃይል እንዳለውም ያምን ነበር (Gill, 2010)። ነገር ግን መለስ በዋናነት የሚያምንበት ነገር በኢትዮጲያ ውስጥ ያለው የልማታዊ መንግሥት ቅርጽ የሀገሪቱን አውድ እና ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ እንደሆነ ያስረዳል (Zenawi, 2012; de Waal, 2012)። በመሆኑም በመርህ ደረጃ የኢትዮጲያ ልማታዊ መንግሥት ዴሞክራሲን እንዲሁም ነጻና አሳታፊ የፖለቲካ ምሕዳርን ባይቃወምም፣ የኢትዮጲያ ነባራዊ ሁኔታና ዐውድ የበለጠ ፈላጭ ቆራጭ የሆነ መንግሥት አስፈላጊነትን እንደሚያሳይ መለስ ያስረዳል።

የእንግሊዝ ዓለም አቀፍ የልማት ክፍል ያረቀቀው የመረጋጋት ግንባታ ማዕቀፍ፣ ዴሞክራሲ በየትኛውም የዓለማችን ክፍል ለሚገኙና በየትኛውም ጊዜ ለሚኖሩ ሕዝቦች አይነተኛው የማስተዳደር መንገድ እንደሆነ ታሳቢ ያደርጋል፤ በዚህም ምክንያት የተለየ ትኩረት ከሚሰጣቸው ነገሮች አንደኛው ፍትሐዊ ምርጫ ነው። ነገር ግን መለስ ዴሞክራሲ እና ልማት አብረው መሄድ አለባቸው የሚለውን ሐሳብ አይጋራውም፤ ''በጽንሰ ሐሰብ ደረጃ ኢኮኖሚያዊ ልማትን ለማምጣት የዴሞክራሲ ግንባታን እንደ ቅድመ ሁኔታ መውሰድ ምክንያታዊነት ይጎድለዋል፤ ባይሆን የዚህ ተቃራኒ ማለትም በተወሰነ መልኩ እድገት ያሳየ የኢኮኖሚ ልማት የዴሞክራሲ ግንባታን ያመጣል የሚለው ሙግት ከቀደመው ይልቅ የተሻለ ነው፤ ነገር ግን ይህም ቢሆን

የተረጋገጠ እውነት አይደለም'' (Gill, 2010, pp. 169–170; Zenawi, 2012)ብሎ ያምናል። እንደ መለስ ራዕይ በማደግ ላይ ላሉ ሀገራት የሚያስፈልገው የረጅም ጊዜ የኢኮኖሚ እቅዶችና መረጋጋት ሲሆን፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም እነዚህ ከዴሞክራሲያዊ ሂደቶች በላይ ቅድሚያ ይሰጣቸዋል። በዚህም መንገድ የሚመጣው እድገት ዴሞክራሲ እንዲያብብ እድልን እንደሚፈጥር መለስ ያምናል (Zenawi, 2012)።

ዴሞክራሲና ልማት ላይ እንዲህ አይነት ሐሳቦችን በማቀንቀን መለስ ብቻውን አልነበረም። በአንጻራዊነት ዴሞክራሲን ሳያሰፍኑ ነገር ግን ስኬታማ የሆኑ ሀገራትን ለአብነት በማንሳት የመንግሥት አስተዳደር ትስስር ከማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ጋር እንጂ ከዴሞክራሲ ጋር እንዳልሆነ አንዳንዶች ያስረዳሉ (Carothers & de Gramont, 2013)። ስለሆነም በዚህ ጽንሰ ሐሳብ መሰረት የልማት ቁልፉ ዴሞክራሲን የመንግሥት አስተዳደር አድርጎ መጠቀሙ ሳይሆን መንግስት ልማትን ለማፋጠን ያለው ቁርጠኝነትና የሀገርንም ሐብት በዘዴ የመጠቀሙ ጉዳይ ነው (Khan, 2007; Evans & Rauch, 1999; Booth, 2012)።

የመለስ ራዕይ ወደ ዴሞክራሲ ለሚደረገው ሽግግር ግልጽ የሆነ የጊዜ ገደብ አያስቀምጥም፤ በተጨማሪም ለዚሁ ሽግግር የሚያገለግሉ መለኪያዎችና የሽግግሩም አካሄዶች ግልጽ አይደሉም (Meles, n.d.)። በ2005 በተደረገው ምርጫ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ያልተጠበቀና ከፍተኛ ውጤት ሲያስመዘግቡ የተረጋጋ ልማታዊ መንግሥት የመመስረቱ ተስፋ ከስሞ በተቃራኒው በፈላጭ ቆራጭ ልማታዊ መንግሥት ተተካ። በዚሁ በ2005 ይህ የመንግሥት አካሄድ ለሁሉም ግልጽ ሆነ፤ አንዳንዶች ግን የዚህን አዝማሚያ ምልክቶች ቀድመው ተመልክተው ነበር። ለምሳሌ በ1994 ኸርበርት ልዊስ እንዲህ ብለው ነበር ''ፕሬዘዳንት መለስ ዜናዊ እና ኢህአዴግ ከአጀማመራቸው ጠንካራ የሞራልና የፖለቲካ ጥንካሬ ቢኖራቸውም በአሁን ወቅት ግን ወደቀድሞው የኢትዮጲያ ባሕላዊ የአገዛዝ መንገድ ማለትም ፈላጭ ቆራጭ የሆነና ከተመረዎቹ ግብዓትም ሆነ ይሁንታ ወደሌለው አገዛዝ ተመልሰዋል'' (Vaughan, 2003, p. 185)። የፖለቲካ ምሕዳሩ እየሰፋ አለመሄዱንና ከጊዜ ወደጊዜም ሰፊና አሳታፊ የመሆን ምንም አይነት ዝንባሌ አለማሳየቱን አንዳንድ ተንታኞች ቀደም ብለው አስተውለው ነበር። እንደ መለስ አተያይና እምነት የሀገሪቱ ፖሊሲዎች የሚወሰኑት በራሱ በኢትዮጲያ መንግሥት ፍላጎቶችና በዋናነትም በሕዝቦቿ ፍላጎት ነው። ይህንንም አካሄድ ግንባር ቀደም በመሆን የሚመራውና የሚጠብቀው አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊው አመራር ሲሆን ሚናውም የማሕበረሰቡን ክፍሎች ማስተባበርና ማደራጀት ነው (Lefort, 2013)። በመሆኑም የአብዮታዊ ዴሞክራሲ መሰረታዊ ጽንሰ ሐሳቦች የፖለቲካዊ ምሕዳርን ባይገድቡም ሕዝቡ የሀገሪቱን አቅጣጫ ለመወሰን አቅመቢስ እንደሆነ ስለሚቆጥር እንዲህ አይነት አስተሳሰቦች ውስንነትን ፈጥረዋል።

ከምርጫ ሥርዓትና ከፖለቲካ ምሕዳርም በተጨማሪ ኀሳብን መግለጽ/ድምጽን ማሰማት መቻል መረጋጋትን በመገንባት ማዕቀፍ ውስጥ አብይ ሚና አለው። በዚህ አግባብ ኢትዮጲያ ደካማ ነች። Freedom House (2018) በሚያወጣው የሀገራት የነጻነት ደረጃ መሰረት ኢትዮጲያ 12/100 አጠቃላይ የነጻነት ውጤት ሲኖራት(0 አነስተኛ ነጻነትን ሲወክል 100 ደግሞ ከፍተኛ ነጻነትን ይወክላል)፤ ይህ ልኬት የፕሬስ ነጻነትንም ያካትታል፤ በዚህም መሰረት ኢትዮጲያ ነጻ ካልሆኑት ሀገራት ተርታ ትመደባለች። የፖለቲካ መብቶችንም በተመለከተ የኢትዮጲያ ደረጃ ጥሩ አይደለም፤ በዚህም መለኪያ የሀገሪቱ ውጤት 4/40 ነው ('የምርጫ ሂደቶች'ን በተመለከተ 1/12፣ 'የፖለቲካ ብዝኃነትና ተሳትፎ'ን በተመለከተ 0/16፣ እና 'በአግባቡ የሚሰራ መንግሥት'ን በተመለከተ ደግሞ 3/12 ውጤቶችን አስመዝግባለች)። የሕዝቦችን ነጻነት በተመለከተ 8/60 በማግኘት

በአንጻራዊነት የተሻለ ውጤት አስመዝግባለች (‘ኃሳብንና እምነትን በነጻነት መግለጽ’ን በተመለከተ 2/16፣ ‘የማሕበራትና የድርጅቶች ነጻነት’ን በተመለከተ 0/12፣ ‘የሕግ የበላይነት’ን በተመለከተ 2/16፣ እና ‘የግል ነጻነትና የግለሰብ መብቶች’ን በተመለከተ 4/16 አስመዝግባለች)። በመረጋጋት ግንባታ ማዕቀፍ መሰረት የልማታዊው መንግሥት መጪውን ጊዜ የተረጋጋ ለማድረግ የጸና መሰረት መገንባት እንዳልቻለ እነዚህ ሦስት አውዶች ማለትም የምርጫ ሥርዓት፣ የፖለቲካ ምሕዳር እና ኀሳብንበነጻነት መግለጽ ያሳያሉ (የኢኮኖሚ ምሕዳሩን በተመለከተ በክፍል 3.2 እንመለከታለን)።

አሳታፊና ሚዛናዊ የሥልጣን መዋቅሮችን መፍጠር በኢትዮጲያ ታሪክ ውስጥ ጉልህ ስፍራ የሚሰጠው ጉዳይ መሆኑን እናምናለን። በ1970 እና 1980ዎቹ የተስተዋሉት ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎችም የመንግሥት ሥርዓት ለውጥ እንዲመጣና በተለይም ለብዙኀኑ የገጠር ሕዝብ ፍትሕ እንዲረጋገጥ ጥሪን የሚያስተጋቡ ነበሩ (Zewde, 2014)። በድጋሚ በ1980 እና 1990ዎቹ የመንግሥት ሥርዓት ለውጥ እንዲመጣ የሚሞግቱ ከፍተኛ ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎችም ነበሩ (Abraham, 1994)። በ1991 የተመሰረተውም የአሁኑ መንግሥት መሪዎች ያነገቡት ዓላማም ‘‘ትግሉ ስኬታማ እንዲሆን የታጋዩን ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ መብቶችና ፍላጎቶች ማገልገል ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን በጊዜ ሂደት የተማርነው መሰረታዊ እውነታ ነው’’ የሚል ነበር (Abraham, 1994, p. 13)። በጊዜው የነበረው የአሜሪካ አቋምም- ‘‘ዴሞክራሲ! በአፍሪካ ቀንድ የምናደርጋቸው ማናቸውም ተግባራት የሚያበረታቱት የዴሞክራሲ መንገዶች ቅቡል እንዲሆኑና ዴሞክራሲ እንዲተገበር ነው’’ ይህንን ያስተጋባ እንደነበር ተዘግቧል (Abraham, 1994, p. 16)። አሳታፊ መንግሥት እንዲመሰረት የተደረገው ትግልም በ1995ቱ የኢትዮጲያ ሕገ መንግሥት ወስጥ ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲካተቱ አድርጓል (Abraham, 1994)። በወታደራዊው መንግሥት (1974 - 1991) ወቅት የነበረው የሕዝባዊ ቅሬታ ዋና ምክንያት ድምጽን ማሰማት ያለመቻል እንዲሁም ‘‘ጸረ-መንግሥት’’ የሚል ስያሜን ከማግኘት ፍራቻ በመንግሥት ላይ የሚታዩትን ድክመቶችና ክፍተቶችን ለመጠቆም አለመቻል ነበር (Abraham, 1994, p.100)። ለወታደራዊ መንግሥቱ ‘‘ፖለቲካዊ ታዛዥነት ከብቃት ይልቅ ዋጋ ነበረው ። የአስተዳደሩ ዋና ትኩረት ቁጥጥርና ክትትል ላይ ስለሆነ ብቃቱና ቅልጥፍናው ውሱን ነበር’’ (Abraham, 1994, p. 112)። በዚህም ምክንያት ‘‘ብዙ ብቃት ያላቸው ኢትዮጲያውያን ሙሉ አቅማቸውን እንዳይጠቀሙ ሁኔታው ተስፋ አስቆራጭ ነበር’’ (Abraham, 1994, p. 113)። ፈላጭ ቆራጭና ጠቅላይ እዝ ተኮር የሆነው አስተዳደር ‘‘ሁሉም የሕብረተሰብ ክፍልን ተጠቃሚ የሚያደርግ ፈጣን ልማትና እድገትን ሊያመጡ የሚችሉ ሂደቶችን ሁሉ አንቆ የመያዝ አዝማሚያ ነበረው’’ (Abraham, 1994, p. 126)። ሁለተኛውንም የመንግሥት ግልበጣ ተከትሎም አንዳንዶች የወታደራዊ መንግሥቱን መለስ ብለው በመመልከት ‘‘እነርሱ (ወታደራዊ መንግሥቱ) ሥልጣን እስከመልቀቅ ቢያደርሳቸውም እንኳ በፈቃደኝነት አዲስ የዴሞክራሲ መዋቅር መፍጠር ነበረባቸው’’ ሲሉ ይሞግታሉ (Abraham, 1994, p. 125)።

እንደ Clapham (2018) ሙግት ኢትዮጲያ ከልማታዊ መንግሥት የአስተዳደር ዘይቤ ማግኘት የምትችለው ጥቅም ተገባደል። እኛም የምናስተጋባው ‘‘ለኢትዮጲያ መንግሥት የወቅቱ አሳሳቢ ጉዳይ ወደተሻለ የአስተዳደር ዘይቤ የመሸጋገር አስፈላጊነትን ነው’’ (Clapham, 2018, p. 1162)። እኛም Clapham ባለው ሀሳብ ላይ በመመርኮዝ ይህ ሽግግር ምን መምሰል እንዳለበት ሰፋ አድርገን እንመለከታለን። ይህ ሽግግር ንቁ የግል ዘርፍ እና የመንግሥት ተጠያቂነት ከመፍጠር በተጨማሪ አሳታፊ የሆነ የመንግሥት አስተዳደር ሊኖረው ያስፈልጋል። የኢትዮጲያ መንግሥት የልማታዊ መንግሥትን ጽንሰ ሐሳብ በመፈትሽ ባለበት በዚህ ወቅት ወደ አሳታፊ የመንግሥት አስተዳደር የሚደረግ ሽግግር መረጋጋትን እና እድገትን ለማምጣት

የሚጫወተውን ወሳኝ ሚና አጽንኦት መስጠት እንወዳለን። ይህም ፍትሐዊና ግልጽ የምርጫ ሥርዓትን እና ሰፊ የፖለቲካ ምሕዳር በመፍጠር ዜጎች ሐሳቦቻቸውንና አመለካከቶቻቸውን እንዲያስተጋቡ እድል መፍጠርን ያካትታል። ነገር ግን እነዚህን አጠቃላይ ምክረ ሐሳቦች ስንሰጥ አዲሱ የመንግሥት አስተዳደር ዘይቤ ምን መምሰል እንዳለበት እንዲሁም ሽግግሩ በምን መልኩ መካሄድ እንዳለበት በዝርዝር ማስቀመጥ የለብንም። ለእነዚህ ጥያቄዎች መልሶችን መፈለግ የሚኖርበት እራሱ የኢትዮጲያ ሕዝብ ነው።




**ሠንጠረዥ 1 -** በመቀነስ ላይ ያለ የተመጣጠነ የምግብ እጥረት እና ድሕነት በኢትዮጲያ (World Bank, 2017)

ማስታወሻ፡- በ2015 በድሕነት የሚኖረው ሕብዝ ብዛት በመቶኛ የተሰላው ከ NPC (2017) ያለውን አሀዝ በመውሰድ ነው

## 3.2. ፍትሀዊና አካታች የኢኮኖሚ ልማት

የአንድ ሀገር ኢኮኖሚ ሲያድግና በእድገቱም ምክንያት የመጡት ጥቅሞች በማሕበረሱብ ውስጥ ላሉ ብዙኃን ቡድኖች ማዳረስ የሚቻልበት ሥርዓት መኖር ፍትሀዊና አካታች (አሳታፊ) የኢኮኖሚ ልማትን ይገልጸዋል። በተጨማሪም በግብርናው፣ በማምረቻውና በንግዱ ዘርፍ ወጪ ፈላጊ ኢንቨስትመንትን ከሥራ ፈጣሪ እና ገቢ ማሻሻያ ፕሮግራሞች ጋር አጣምሮ የያዘ ነው። ለጤናማ የኢኮኖሚ ሥርዓትም ሙስናን እና ‘በድብቅ የሚደረግ የፋይናንስ እንቅስቃሴን’ መዋጋት አስፈላጊ ነው (DFID, 2016, pp. 8–9)።

የኢትዮጲያ ልማታዊ መንግሥት ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ እድገት አስመዝግቧል። ከ2003 ጀምሮ አጠቃላይ የሀገሪቱ የእድገት መጠን (GDP) ከ 7.6% እስከ 12.6% ተመዝግቧል (ከዓለም ባንክ እና ከኢትዮጲያ መንግሥት ጨምሮ ከተለያዩ መንጮች የተወሰዱት እነዚህ አሃዞች እንደምንጫቸው ልዩነት አላቸው (Cochrane & Bekele, 2018))። ነገር ግን

የኢትዮጲያ መንግሥት በማክሮ ኢኮኖሚው ላይ የሰጠው ቅድሚያ እና ትኩረት ዋጋም አስከፍሎታል። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (UN) የኢትዮጲያ ልማት አካታች ወይም አሳታፊ እንዳልሆነ ይሞግታል (UN, 2015)። በኢትዮጲያ የኢኮኖሚ እድገት እና የኢኮኖሚ ጥቅም ተካፋይነት አብረው መተግበር አልቻሉም፤ እነዚህ ደግሞ የመረጋጋት ግንባታ ማዕቀፍ ሁለት ወሳኝ ዘርፎች ናቸው። የኢኮኖሚ ጥቅም ተካፋይነት ሰፊውን የሕብረተሰብ ክፍል እንዲያዳርስ የድሃው የኑሮ ለውጥ ላይ ያተኮሩ የሕግና የፖሊሲ ማዕቀፎችን ማርቀቅና መተግበርን ይጠይቃል።

የኢትዮጲያን ኢኮኖሚ ልማት በተመለከተ ነባራዊውን ሁኔታ ያልተረዳን ኃሳባውያን አይደለንም። ኢትዮጲያ የሀገር ውስጥ ገቢ እጥረት ስላለባት የውጪ ኢንቨስትመነት ያስፈልጋታል (NPC, 2016)። ቀጥተኛ የውጪ ኢንቨስትመንትን መሳብ ደግሞ ዋጋ ያስከፍላል። መለስ ይህንን በአግባቡ በመረዳቱ ኢትዮጲያ ለውድድር ብቁ የሚያደርጋትና ልቀት የሚሰጣት ተፈጥሮአዊ ቁመና እንደሌላት ይናገራል (Zenawi, n.d., 2012)። የግሉ ዘርፍ ማደግ ለኢኮኖሚያዊ ልማት እጅጉን እንደሚያስፈልግ እንዲህ ቢታመንበትም ነባራዊ ሁኔታው ለመስራት የማያመችና ውሱን ነው። በዓለም ባንክ 11 የሀገራት የሥራ ቅልጥፍና መለኪያዎች ኢትዮጲያ ከዓለም እንዲሁም ከሰሀራ በታች ካሉ ከአፍሪካ ሀገራት ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች (World Bank, 2018)። በዚህም መለኪያ መሰረት ሀገሪቱ አዲስ ሥራ/ንግድን ለመጀመር ያለውን ቀልጣፋ አሰራር በተመለከተ ከ 190 ሀገራት 174ኛ፣ የግንባታ ፋቃድ ጉዳዮችን በተመለከተ 169ኛ፣ የኤሌክትሪክ አቅርቦትን በተመለከተ 125ኛ፣ ንብረትን በማስመዝገብ ጉዳዮች 139ኛ፣ ብድርን የማግኘት ቅለትን በተመለከተ 173ኛ፣ ለአነስተኛ ኢንቨስተሮች ጥበቃ በማድረግ 176ኛ፣ድንበር ተሻጋሪ ንግዶችን በተመለከተ 167ኛ፣ ውሎች እንዲተገበሩ ማስገደድን በተመለከተ 68ኛ እና ለውዝፍ ብድሮች መፍትሔ በማበጀት 12ኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች። የኢትዮጲያ መንግሥት ምንም እንኳ የተወሰኑ አይነት የውጪ ኢንቨስትመንቶችን ለመሳብ ፍላጎት ቢኖረውም፣ በሀገር ውስጥ ይህንን ለመስራት የሚያስችል ምቹ ሁኔታዎች አለመፍጠሩን እነዚህ አሃዞች ይጠቁማሉ (ድብቅ የገንዘብ ዝውውሮችን በተመለከተ በክፍል 3.5 እንመለከታለን)።

በኢትዮጲያ የኢኮኖሚ እድገት፣ የኢኮኖሚ ጥቅም ተካፋይነትና አሳታፊ የኢኮኖሚ ልማት ውስብስብ ጉዳዮች እንደሆኑ ለመረዳት በሀገሪቱ ያለውን የድህነት ሁኔታ መመልከት ጥሩ እይታን ይሰጣል። ድህነት መላው ኢትዮጲያን የሚያዳርስ ችግር ነው። ነገር ግን ድህነትን የተመለከቱ ጥናቶች በአካሄዳቸውም ባገኙት ውጤትም ይለያያሉ። 71.1% ኢትዮጲያውያን በጽኑ ድህነት ውስጥ እንደሚኖሩ የኦክስፈርድ የድህነትና የሰው ሐብት ልማት ተቋም የ2011ን መረጃ በመጠቀም ይዘግባል (OPHI, 2017)። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰው ሐብት ልማት ሪፖርት ደግሞ 67% ኢትዮጲያውያን በጽኑና ዘርፈ-ብዙ ድህነት ውስጥ እንደሚኖሩ ሲዘግብ (UNDP, 2017)፤ የዓለም ባንክና የኢትዮጲያ መንግሥት በድህነት ውስጥ የሚኖረው ሕብረተሰብ ቁጥር የዚህ አሃዝ ግማሽ አካባቢ እንደሆነ ይናገራሉ (ሠንጠረዥ 1ን ይመልከቱ) (NCP, 2017; World Bank, 2017)። በአሁኑ ወቅት ከ100 ሚሊዮን በላይ የሚሆነው የሀገሪቱ ሕዝብ አሁንም በፍጥነት እየጨመረ ቢሆንም የተገኙት መረጃዎች እንደሚጠቁሙት በድህነት ውስጥ የሚኖረው ሕዝብ ግን እየቀነሰ እንደሆነ ነው (ሠንጠረዥ 1)። ነገር ግን ንኡስ-ብሔራዊ ልዮነቶች በእንደዚህ አይነት ጥቅል ብሔራዊ መረጃዎች ሊደብቁ ይችላሉ። ይህም የሚሆነው የክልሎች የድህነት ደረጃ በየጊዜው ልዩነት ሲኖረውና የድህነት መቀነሱም በየጊዜው በእኩል መጠን ሳይሆን ሲቀር ነው (UNDP, 2015)። በተጨማሪም በአጠቃላይ የሁሉም ዓለም አቀፍ ድረጅቶች (ማለትም የዓለም የጤና ድርጅት (WHO)፣ የአሜሪካ ዓለም ዓቀፍ የልማት ድርጅት (USAID)፣ የተባበሩት መንግሥታት የሕጻናት መርጃ ድርጅት (UNICEF)፣ እና የዓለም ባንክ) የመረጃ ምንጭ የሚወሰደው በዋናነት

ከመንግሥት ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ነው። በኢትዮጲያ መንግሥትና በዓለም ባንክ እንዲሁም በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መካከል ያለው የመረጃ ልዩነት የሕዝብ ብዛት ላይ ነው፤ ይህም የነፍስ ወከፍ እድገትን ከፍ የማድረግ አቅም ስላለው አጠቃላይ ሀገራዊ እድገቱ ከፍተኛ አድርጎ የማሳየት እድል ይፈጥራል ።

የኢትዮጲያየድህነት ምጣኔና የተመጣጠነ ምግብ እጥረት ሁኔታ በአለም አስከፊ ከሚባሉት ተርታ የሚመደብ ቢሆንም፤ እነዚህን ችግሮች በመቀነስ ረገድ ሀገሪቱ ያሳየችው እመርታ የህዝብ ቁጥር እድገቱ እመርታ እያሳየ ባለበት ወቅት መሆኑ በተወሰነ መልኩም ቢሆን የፍትሀዊ ተጠቃሚነት ሁኔታ ጥረት መኖሩይጠቁማል ። ከ1980 ጀምሮ የነበረው የሕዝብ ብዛት ከ 35 ሚሊዮን ወደ 100 ሚሊዮን በማደግ በሦስት እጥፍ ገደማ ጨምሯል (UN, 2011, 2015)። በሠንጠረዥ 1 በሚታዩት አሃዞች የሕዝብ ብዛት በመቶኛ የተቀመጠ ሲሆን መጠኖቹን መቀነስ የተቻለው በዚሁ ወቅት የኢትዮጲያ የሕዝብ ብዛት በዓለም በከፍተኛ መጠን እያደጉ ከሄዱት አንዱ በሆነበት ጊዜም ነው (World Bank, 2017)።

የሚሊኒየሙ የልማት ግቦች በድህነትና በተመጣጠነ የምግብ እጥረት የሚጠቃውን ሕዝብ ለመቀነስ ሀገራት የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ የሚደግፉ ነበሩ (Bluffstone, Yesuf, Bushie, & Damite, 2008; Brown & Teshome, 2007)። የዘላቂ የልማት ግቦች ግን ከቀደመው ለየት የሚሉ ናቸው። የእነዚህ ግቦች ትኩረት በችግር የሚጠቁትን ሕዝቦች መቀነስ ብቻ ሳይሆን ድህነትንና ችጋርን ጨርሰው ለማጥፋት የታለሙ ናቸው። የተገኙት መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ፈላጭ ቆራጭ የሆነው ልማታዊ መንግሥት አቅሙን በማሳደግ፣ ተደራሽነቱን በመጨመርና የተለያዩ ተግባራትን በማከናወን ከላይ የታዩትን ቅነሳዎች አሳክቷል፤ በተጨማሪም እነዚህ ለውጦች የመጡት መንግሥት ሐብትን በማሰተባበር፣ መረጋጋትን በመፍጠርና የረጅም ጊዜ እቅዶችንም በመያዙ ነው። ይህም ለሚሊኒየሙ የልማት ግቦች ስኬት እጅጉን ጠቅሟል። የዘላቂ የልማት ግቦችን ለማሳካት ደግሞ ለውጡ ከብዛት (ማለትም ተደራሽነት፣ መረጋጋትና ሐብትን ማስተባበር) ወደ ጥራት መሸጋገር ያስፈልገዋል፤ ይህም መሳካት የሚችለው ስኬታማነትንና ቅልጥፍናን በከፍተኛ መጠን በመጨመርያልተመጣጠነእድገትና የሀብት ልዩነት በተንሰራፋበት ሀገር (Cochrane & Rao, 2019; OPHI, 2017) ‘‘ወደ ኋላ የሚቀር ማንም ሰው መኖር የለበትም’’ የሚል ግብን በመሰነቅ ነው። በጠቅላላው አሳታፊ ልማትን ለማምጣት አዲስ አካሄድ ያስፈልጋል።

ልማታዊ መንግሥቱ ማክሮ ኢኮኖሚው ላይ ትኩረት በመስጠቱ የተፈጠረውን ያልተመጣጠነእድገትና የሀብት ልዩነት በጥቂቱ እንመልከት። ያልተመጣጠነእድገትን በአግባቡ ለመረዳት የመረጃዎችን ስብጥር አካቶ የያዘው በዓለም የጤና ድርጅት የተዘጋጀው ጠንካራ መለኪያ ነው፤ ይህም መለኪያ በ Cochrane and Rao (2019) በአግባቡ ተገምግሟል። ሰፊ የሆነ የሕጻናት ጤንነት መለኪያዎችን በመጠቀም ከስነ-ጾታ፣ የመኖሪያ አካባቢ (ገጠር ወይም ከተማ)፣ የኢኮኖሚ ደረጃ፣ የትምህርት ደረጃ፣ ብሔር፣ እና ፖለቲካ ጋር የተያያዙ ወሳኝ መለኪያዎችን በመጠቀም ያልተመጣጠነእድገትሁኔታን ይመለከታሉ። በዋናነትም እነዚህ ያልተመጣጠነእድገትተጋላጭነቶች በመደራረብ ለብዙ ቀጣይ ተጋላጭነቶችና መበላለጦች ሊዳርጉ እንደሚችሉ በ Cochrane እና Rao ጥናት ትኩረት ተሰጥቷቸዋል። እነዚህ ተደራራቢ ተጋላጭነቶች ላይ ትኩረት ሰጥቶ የዳሰሰው ሌላ ጥናት በ Husmann (2016) የተደረገ ሲሆን ይህም ጥናት እነዚህ ተጋላጭነቶች ከኢትዮጲያ ማሕበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ የሥነምህዳርና እና መልካምድራዊ ሥርአቶች ጋር ያላቸውን ግንኙነቶች የሚዳስስ ነው። ይህም የ Husmann ጥናት መበላለጥን ለመፈተሽ የምንጠቀምባቸው ግብዓቶችና የዚህ ዓይነት ጥናት ውጤቶች ምን ያህል ውስብስብ እንደሆኑ ያሳየናል። የኦክስፈርድ

የድህነትና የሰው ሐብት ልማት ተቋም አካባቢ ተኮር የድህነት ጥናት (የገጠር፣ ከተማና ክልሎችን) በማድረግ ያገኘው ውጤት ከፍተኛ ልዩነቶችን አግኝቷል (OPHI, 2017) ። በዚህም መሰረት በገጠር የሚስተዋለው ድህነት ከከተማው በአራት እጥፍ ይበልጣል። ጥናቱ ሰፊ ክልላዊ ልዩነቶችንም አግኝቷል፤ በኢትዮጲያ 'የብሔር ፌደራሊዝም' የክልሎች አወቃቀር መሰረት እነዚህ ልዩነቶች የመልከአምድራዊ ብቻ ሳይሆኑ የብሔርና የቋንቋንም ልዩነት ያካትታሉ። ለምሳሌ በአፋር ውስጥ በጽኑ ድህነት የሚኖረው የሕዝብ ቁጥር በመቶኛ ሲሰላ(79.7%) ከሐረሪው(36.6%) እና ከድሬደዋው(38.5%) በሁለት እጥፍ ሲበልጥ በጋምቤላ(57.5%) ካለውም በላይ ከፍተኛ ነው።

እየተለመደ በመጣውና በልማታዊ መንግሥት ቅርጽ በተነደፈው የኢኮኖሚ ልማት ሳቢያ የመጡትን ተግዳሮቶች ከግንዛቤ በማስገባት በ2018 ወደ ስልጣን የመጣው ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አሕመድ መንግስት የአሳታፊ ልማት ደጋፊ በመሆን ይታወቃል። የቀደሙትን የትኩረት አቅጣጫዎች በመፈተሽ መንግሥት የልማት አጀንዳው ላይ የትኩረት ችግር ሳይኖረው እንዳልቀረ ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አሕመድ ጠቁሟል። በተለይም በትላልቅ የመሰረት ልማት አውታሮች ላይ የሚውለውን ብዙ ቢሊየን ዶላር ወጪ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ መሰረታዊ የመስኖ ልማት ላይ በማዋል የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ይቻል እንደነበርም አሳስቧል[2]። ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አሕመድ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሰጠውና በሰኔ ወር ላይ በተላለፈው የቀጥታ ሥርጭት መልእክቱ የምክር ቤት አባላት በመጡባቸው አካባቢዎች የመሰረታዊ የመስኖ ልማት ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ አሳስቧል። ይህንን አዲስ የትኩረት አቅጣጫ በጀት በመመደብና ሀገሪቱን መግቦ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ትኩረት እንደሚሰጠው አጠንክሮ ተናግሯል። ''(ለ2018/19 ከሚመደበው በጀት ውስጥ) 64% የሚሆነው እንደ ትምህርት፣ ጤና፣ ውሃ እና መሰል ድሃ-ተኮር መርሐ ግብሮች ላይ ይውላል'' በማለት ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አሕመድ ተናግሯል፤ ይህም መጠን ከሌሎች አፍሪካ ሀገራት አንጻር ከፍተኛው ነው (ENA, 2018)። እነዚህ ምልከታዎችና አዲስ አቅጣጫዎች የቀደመውን የአስተዳደር መንገድ በተለይም ጉድለቶቹን መመልከት እንድንችል ረድቶናል።

## 3.3 ግጭትን የመፍቻ መንገዶች

ግጭትን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የሚያስችሉ ዘመናዊና ባሕላዊ አካሄዶች ሁሉ ግጭትን የመፍቻ መንገዶች ውስጥ ይጠቃለላሉ። የእንግሊዝ ዓለም አቀፍ ልማት ክፍል ማዕቀፍ ቅድመ ግጭት፣ የግጭት ጊዜና ድሕረ ግጭት የአፈታት መንገዶችን አካቷል፤ ከእነዚህም ውስጥ 'ቅድመ ጥንቃቄ'፣ 'ፈጣን ማገገም'፣ እና 'ዜጎችን የማግባበትና የማወያየት ተነሳሽነቶችን'ም ያጠቃልላል (2016, pp. 10–11)። በኢትዮጲያ ያሉ 'ዘመናዊ'ም ሆነ 'ባሕላዊ' የግጭት አፈታት መንገዶች ዘርፈ-ብዙ ናቸው፤ የእያንዳንዱ ሂደትም ሆነ ዓላማ የተለያየ ነው። እንደ Bouh and Mammo አገላለጽ ''የተለያዩ ባሕሎች ግጭትን ለመቆጣጠር ብዙ ዓይነት መንገዶችን ይጠቀማሉ'' (2008, p. 109)፤ ኢትዮጲያውያንም እጅግ የበዙና ስኬታማ ግጭትን የመፍቻ መንገዶች አሏቸው። የፌደራላዊ መንግሥቱም እነዚህን ባሕላዊ መንገዶች በተወሰነ ደረጃ ጥቅም ላይ ሲያውላቸው ይታያል። ነገር ግን መንግሥት የራሱ የሆነ መደበኛ አካሄድ ሲኖረው ይህም በተለይ ከልማታዊ መንግሥት ጽንሰ ሐሳብ ጋር የተገናኘ ነው።

---

[2] ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አሕመድ ብዙ ጊዜ በመገናኛ ብዙኃን ሽፋን ያገኙ ንግግሮችና መግለጫዎች ሰጥ ቷል። አብዛኛዎቹ እነዚህ ንግግሮች በአማርኛ የተደረጉና በቴሌቪዥን ወይም/እና በሬዲዮ የተሰራጩ በመሆናቸው በጽሁፍ ወይም በድረ-ገጾች ላይ አይገኙም። በዚህ ምክንያት ይህንን ምንጭ ለማጥቀስ አስቸጋሪ ያደርገዋል። በጠቅላይ ሚኒስትር አብይ የተሰጠው ይህ አስተያየት በደቡብ ሬዲዮ F.M. 100.9 በሰኔ19 2018 የተላለፈ ነው።

የኢትዮጲያ ልማታዊ መንግሥት ያጋጠመውን ከጎረቤት ሀገር ኤርትራ ጋር ያለውንና ለረጅም ጊዜ የቆየውን በሀገራት መካከል የተከሰተውን ግጭት አንድ ምሳሌ መውሰድ እንችላለን። ይህንን ግጭት ለመቀነስ አለም-አቀፍ ሰላም አስከባሪ ግብረ-ኃይል ወደ አካባቢው መሰማራቱ ይታወሳል (Cliffe, Love, & Tronvoll, 2009; Abbink, 2003a, 2003b)። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ባድመ ለኤርትራ እንድተሰጥ መወሰኑ ጦርነቱ ወደ ከፍተኛ ደረጃ እንዲደርስ ያደረገው ዋና ምክንያት ነው። መለስ እና ፓርቲው ይህንን ውሳኔ ‘‘ትርጉም የማይሰጥ የሕግ ውሳኔ’’ (Cliffe, Love, & Tronvoll, 2009, p. 154) በማለት ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ውሳኔ ለመገዛት ምንም ጥረት አላደረጉም፤ ግጭቱንም ለመፍታት ሌላ አማራጭ አልፈለጉም። ልማታዊ መንግሥቱ እራሱ በፈለገው መንገድ ሊሄድ ያልቻለውን ውሳኔ ሳይቀበል አስር ዓመት ካለፈው በኋላ ድጋሚ ጦርነት የመቀስቀሱ ፍርሃት አንዣቦ ነበር። የልማታዊ መንግሥት ጽንሰ ሐሳብ በራሱም ሆነ በጎረቤት ሕዝቦች ላይ የራሱን አቋም ለመጫን እንደሚፈልግ ይህ አንዱ ማሳያ ነው። እንዲህ ዓይነቱም መደበኛው የመንግሥት ግጭትን የመፍቻ መንገዱ ስኬታማ አልሆነም።

በሀገር ውስጥም ቢሆን በኢሕአዴግ በሚመራውና በኢትዮጲያ ውስጥ ባለው ልማታዊ መንግሥት ስር ያለው የፍትሕ ሥርዓት ፖለቲካዊ አድሎአዊነት እንደሚታይበት ይተቻል፤ ከዚህም ባለፈ ግጭቶችን ለራሱ ጥቅም በሚያስገኝ መልኩ እንደሚያነሳሳ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ታምራት ላይኔ አረጋግጧል[3]። ይህም የአሁኑን አመራር ትኩረት በመሳቡ አጠቃላይ የፍትሕ ዘርፉን ለማሻሻል የሚሰራ ኮሚቴ ተቋቁሟል (Ayele, 2018)። በ2018ም አስከፊ በሆኑት የማቆያ ጣቢያዎችና እንደ ቃሊቲ፣ ሸዋሮቢት፣ እና ድሬደዋ ባሉት ብዙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች እንደሚፈጸሙ በሚነገሩባቸው ማረሚያ ቤቶች ውስጥ የሚሰሩትን አስተዳደሮች ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አሕመድ በሌሎች ቀይሯቸዋል። እነዚህ ለውጦች የልማታዊውን መንግሥት የቀድሞ የአካሄድ ክፍተቶች ይጠቁማሉ፤ በተለይም ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት አለመቻሉን አስረጅ ናቸው።

በግንባር ቀደሙ አመራር ውስጥ የተደረገውም ማሻሻያ ይህን ለውጥ አምጥቷል። አዲሱ በጠቅላይ ሚኒስትር አብይ የሚመራው መንግሥት ከኤርትራ ጋር ሰላምን ለማድረግና የአልጀርስ ስምምነትንም ለመቀበል (ይህ ስምምነት የተፈረመው በ 12 ሕዳር 2000 ነው) ተግባራዊ እንቅስቃሴ አድርጓል። በሁለቱ ሀገራት መካከል ለተደረገው ስምምነት የጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አሕመድ ወዳጅነት የተሞላበት አካሄድ ምስጋና ተችሮታል (The Economist, 2018)። መሪዎቹ በሁለቱም ሀገሮች ታሪካዊ ጉብኝቶችን አድርገዋል። የኢትዮጲያና የኤርትራም አየር መንገዶች አቋርጠውት የነበረውን ወደ ሁለቱም ሀገሮች የሚደረጉትን በረራዎች ጀምረዋል (Reuters, 2018; Mohammed, 2018)። ጠቅላይ ሚኒስትር አብይም ከሁሉም ጎረቤት ሀገሮች ጋር በሰላምና በመግባባት አብሮ ለመኖር፣ እና ‘‘የአፍሪካ ቀንድ ደኅንነት’’ ላይ ትኩረት ያደረገ ‘‘ሁሉም አሸናፊ’’ የሚሆንበትን የኢኮኖሚ ግንኙነት ለመፍጠር ጥሪ አቅርቧል (Government Communication Affairs, 2018)። የመረጋጋት ግንባታ ማዕቀፍን ታሳቢ በማድረግ የኢሕአዴግ ልማታዊ መንግሥት በሀገር ውስጥም ሆነ በውጪ ግጭትን በመፍታት ስኬታማ አልነበረም፤ ስኬታማ ከተባለም ግጭቶችንም ‘ለመፍታት’ የተጠቀመበት መንገድ የራሱን ውሳኔና አቋም በሌሎች ላይ በመጫን ነበር። በ2018 የመጣው የፖለቲካ አካሄድ ለውጥ ግጭትን ከመፍታት ጋር የተያያዙት እነዚህ ጉድለቶች ከሰፊው የልማታዊ መንግሥት ጽንሰ

[3] የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ይህንን ቃለ-መጠይቅ ያደረገው በነሐሴ 2፤ 2018 በ ናሁ ቲቪ (ምን ይላሉ? በሚሰኝ ፕሮግራም) ላይ ነው። የቴሌቪዥን ጣቢያው ይህንን ቃለ መጠይቅ በድረ ገጹ ላይ አላሰፈረውም። የቃለ መጠይቁ ቅጂዎች በ YouTube ላይ ይገኛሉ። እነዚህ ቅጂዎች በናሁ ቲቪ ፍቃድ የተጫኑ ስለማይመስሉ የቅጂዎቹን ማስፈንጠሪያዎች አላካተትናቸውም።

ሐሳብ ጋር እንዴት እንደተቆራኙ ያሳያል። መንግሥትም ይህንን ጽንሰ ሐሳብ በመፈተሹና በመመርመሩ ምክንያት በመተባበርና በመግባባት ላይ የተመሰረቱ ግጭትን የመፍቻ አካሄዶችን መጠቀም ከማስቻሉም ባለፈ ከልማታዊ መንግሥት ጽንሰ ሐሳብ ጋር የተያያዙ ብዙ ጉዳዮችንም ጥያቄ ውስጥ እንዲገቡ አድርጓል።

## 3.4. ስኬታማና ሕጋዊ ተቋማት

ሕጋዊ ተቋማት በ''ሕጋዊ መንግሥት'' ጥላ ሥር ያሉና የሕዝቡን ይሁንታ ያገኙ የ ''ሕዝብ ባለሥልጣናት'' ናቸው። ይህንን በተመለከተም መረጋገጥ ያለባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች ደሕንነት፣ የሕግ የበላይነት፣ ፍትሕ፣ እና መንግሥትም ሆነ መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት የሚሳተፉበት ስኬታማ የ''ማክሮ ኢኮኖሚ አስተዳደር'' ናቸው (DFID, 2016, pp. 12–13)። እንደ Naqvi (2018) ሙግት የምስራቅ እስያ ልማታዊ መንግሥታትን ስኬት በመመልከት ብቻ የእነሱን የመንግስት አስተዳደር ፈለግ መከተል አይገባም፤ ምክንያቱም ሙስና ተንሰራፍቶባቸውና የመንግሥታቸውም አቅም ሲፈታተነው እንመለከታለን። በዚህም መሰረት ተቋማት ስኬታማ እንዲሆኑ ብቃት እና የሕዝብም ይሁንታ እንደሚያስፈልጋቸው Naqvi (2018) በልማታዊ መንግሥታት ላይ ያደረገው ምልከታም ሆነ የመረጋጋት ግንባታ ማዕቀፍ አንድ አይነት አተያይ አላቸው።

በኢትዮጲያ መንግሥት የተዘጋጀውና በዘላቂ የልማት ግቦች ላይ ያተኮረው ሪፖርት እንደሚያሳየው ስኬታማና ሕጋዊ ተቋማት መፍጠር አመራርን ብቻ የሚመለከት ጉዳይ አይደለም (NPC, 2017)፤ የቴክኒክ ብቃትም/አቅምም ይፈልጋል። ይህ አይነቱ ትርክት አዲስ አይደለም፤ ''አቅም ግንባታ'' እና ''መልካም አስተዳደር'' የኢትዮጲያ መንግሥት ለረጅም ጊዜ የሚጠቀምባቸው ቃላት ሲሆኑ ሐብትን ለመሳብ እና የራሱን አጀንዳ በማራመድ ''ስኬታማ'' ልማታዊ መንግሥት ለመመስረት ደጋግሞ የሚያነሳቸው ኃሳቦች ናቸው (Fantini, 2013)። የኢትዮጲያ መንግሥት የሲቪል ማሕበራትን በመዝጋትና ከዛም በተጓዳኝ ዓለም አቀፍ ድጋፍን ለማግኘት የ''አቅም ግንባታ'' ፍላጎት በማሳየት፤ የልገሳ የድጋፍ ገንዘብን ተጠቅሞ የራሱን አጀንዳ ለማራመድ አውሎታል። በዚህም መንገድ የመንግሥት መዋቅራትንና በውስጡም ያሉትን ሠራተኞች ይህንን አጀንደ ማስፈጸሚያ አድርጓቸዋል።

በ1990ዎቹ መጀመሪያ የጋራ ሕብረትን በማቋቋም አሁን በስልጣን ላይ ያለው መንግሥት ሲመሰረት በሦስት ዋና አቅጣጫዎች ላይ ማሻሻያዎችን ለማድረግ ቃል ገብቶ ነበር፤ እነርሱም (ሀ) የብሔር ፌደራሊዝምን መሰረት በማድረግ የሥልጣን ክፍፍል ማድረግ (ለ)የፓርቲ ስብጥርን በማረጋገጥ ነጻና ፍትሐዊ የምርጫ ሥርዓት መገንባት (ሐ)ኢኮኖሚውን ነጻ ማድረግ (Vaughan 2015, cited in Harald Sande Lie & Mesfin, 2018, p. 9)። ልማታዊው መንግሥት እነዚህን ማሻሻዎች የማድረጉ ጉዳይ ግን አሁንም አጠያያቂ ነው (Lefort, 2013; Abbink, 2017)። የምርጫ ሥርዓት በክፍል 3.1 ስለተዳሰሰ በዚህ ክፍል የምናተኩረው በተቋማትና የተመሪውን ሕዝብ ይሁንታ የማግኘታቸውን ልክ ነው።

እንደ Harald Sande Lie and Mesfin (2018, p. 4) ምልከታ ''በ 'ዴሞክራሲያዊ ልማታዊ መንግሥት' ስር ተወዳዳሪ እና ተቃራኒ ቅሬታዎችን መቆጣጠር ከባድ ነው''። ተወዳዳሪ እና ተቃራኒ ቅሬታዎች ባሉበትም የተመሪዎችን ይሁንታ ማግኘት አዳጋች ይሆናል። ሕዝቡ በአውራው ፓርቲ መጠበቅአለበት የሚልና መንግሥትም በሕዝቡ ፈንታ ውሳኔ መስጠት እንዳለበት የሚያስቀምጥ የጽንሰ ሐሳብ መሰረት መኖሩ ደግሞ ይህንን ጉዳይ የበለጠ ውስብስብ ያደርገዋል። በ2014 ተቃውሞዎች

በርትተው ወደ አደባባይ መውጣት በጀመሩበትም ወቅት ልማታዊ መንግሥቱ ኃይልን ከመጠቀም ባለፈ እነዚህን ቅሬታዎች መልክ ሊያሲዝ የሚችልበት መንገድ አልነበረውም (Kestler and D'Amours, 2018; BBC News, 2016)። ሰኬታማ ያልሆኑ ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች አሳታፊ ያልሆነ የመንግሥት ሥርዓት ውጤት መሆናቸውን የኢትዮጲያ ታሪክ በግልጽ እንደሚያሳይ እናምናለን፤ ይህም የብዙኃኑ ቅሬታ ዋና ምክንያት ነው። ልክ በ1960 እና 1970ዎቹ እንዲሁም በ1980 እና 1990ዎቹ እንደነበሩት በአሁኑም መንግሥት ላይ የተስተዋሉት ከፍተኛ ሕዝባዊ አመጾች ዋነኛ ምክንያቶች ሥር የሰደደው ያልተመጣጠነ እድገት/ ፍትሀዊ ያልሆነ የሀብት ክፍፍል ና ፈላጭ ቆራጭ የሆነው የአገዛዝ መንገድ ናቸው። በ2016 ሀገሪቱ ብዙ ሕዝባዊ ተቃውሞዎችን በየቦታው አስተናግዳለች። ሕዝቡ ጠንከር ያሉ መንገዶችን መምረጡ ግር ሊያሰኝ አይገባም። ነገር ግን ከ2005 ጀምሮ በፋላጭ ቆራጭ  ልማታዊ መንግሥት ስር በመሆኑና ተቃውሞውም ድምጹ ያለመሰማቱ ነጸብራቅ እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል።

ከ መስከረም 2018 በኋላም ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ የልማታዊ መንግሥትን ጽንሰ ሐሳብንም ሆነ አካሄድ አላስተባበለም። ነገር ግን በእርግጠኝነት አዲስን መንገድ እየተከተለ ይመስላል። መንግሥት የተመሪው ሕዝብን ይሁንታ ባለማግኘቱ ምክንያት በመንግሥት ተቋማት ላይ ተዓማኒነት የለም። ለውጡም ይህንን መሰረት አድረጎ እየተንቀሳቀሰ ነው። ለብዙ ተቃዋሚ የፖለቲካ መሪዎችና ጋዜጠኞች እሰር ምክንያት የሆነውን አና አከራካሪውን የጸረ-ሽብር አዋጅ የፍትሕ ሥርዓቱ ሲተግብር ቆይቷል። አሁን ግን መንግሥት የፖለቲካ ታራሚዎችን ከእስር መልቀቅን ጨምሮ ሀገር አቀፍ ማሻሻያዎችን በማድረግ ላይ ይገኛል። በተጨማሪም አዲሱ መንግሥት በደህንነት ቢሮውም ላይ ማሻሻያዎችን አድርጓል፤ ይህ ቢሮ የገዥው ፓርቲ የጭቆና መሳሪያ በመሆኑ ይወነጀል ነበር። በ2020ም ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ እንደሚደረግ ቃል ገብቷል። በቅርብ የሚስተዋሉት እነዚህ ለውጦች ልማታዊ መንግሥት አንደ አንድ መንግሥት አስተዳደር መንገድ ስኬታማ ያልሆነባቸውን አቅጣጫዎች አጉልተው በማሳየት በሕዝባዊ ድጋፍና ይሁንታ የተመሰረተ አዲስ አካሄድ እንደሚያስፈልግ ጠቋሚ ናቸው።

## 3.5 በትብብር ላይ የተመሰረተ  የቀጠና ከባቢን መፍጠር

ይህ አውድ የሚወክለው ሀገራት ወይም ማሕበረሰብ ከእነሱ ውጪ ያለን ከባቢ ጥቅም ላይ በማዋል ጉዳቶችን የመቋቋም አቅማቸውን ነው። ይህ የመረጋጋት ግንባታ ማዕቀፍ አውድ ከጎረቤትና ከዓለም አቀፍ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር ቀና ግንኙነት ከማድረግ ባለፈ ሽብርን እና ሌሎች ሁከት-ተኮር ‘‘የሽብር ጽንሰ ሐሳቦችን’’፣ እና ዓለም አቀፍ የወንጀል እንቅስቃሴዎችንና ‘‘ድብቅ የገንዘብ ዝውውሮችን’’ መከላከልን ያጠቃልላል (DFID, 2016, pp. 14–15)።

የአፍሪካ ቀንድ ሠላምና መረጋጋት የሰፈነበት የዓለማችን ክፍል አይደለም። ሁለቱ የኢትዮጲያ ጎረቤቶች ደቡብ ሱዳን እና ሶማልያ ሀገር ለመሆን ብቁ ያልሆኑ መንግሥታት ናቸው። ኤርትራም እሰከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የኢትዮጲያን መንግሥት የሚዋጉ አማጽያንን ስታስተናግድ ቆይታለች። ባለፈው አስር ዓመት ውስጥ በሶማሊያ ውስጥ ያለውን ሽብርተኝነት ለመዋጋት ኢትዮጲያ ብዙ ጊዜ ተሳትፋለች። ኢትዮጲያ 80% የሚደርሰውን የአባይ ወንዝ ምንጭ ከመሆኗ ጋር ተያይዞም የሐብት መጋራት ግጭቶችም ተስተውለዋል (Harald Sande Lie & Mesfin, 2018)። ከ6000 ሜጋ ዋት በላይ ኃይል አንደሚያመነጭ ከሚጠበቀውና በአፍሪካም ትልቁ ከሆነው የውሃ ኃይልን የሚጠቀመው ግድብም ጋር በተያያዘ ግብጽ በኢትዮጲያ መንግሥት ላይ ያላትን ጠንካራ ተቃውሞ ከመግለጽም አልፋ በአንድ አንድ ወቅቶች ኢትዮጲያ ለብሔራዊ ደህነቷ ስጋት መሆኗንም ገልጻለች (Lie, 2010; Whittington, Waterbury, & Jeuland, 2014)። ፈጣንና ቀደም ያሉ ድርድሮች ተደርገው ቢሆን እነዚህ ውጥረቶችም በረገቡ

ነበር (Whittington et al., 2014)። ነገር ግን የልማታዊ መንግሥት የጽንሰ ሐሳብ መሰረት በድርድርና በትብብር ስምምነቶችን ከማድረግ ይልቅ ሞገደኛና አቅምን በኃይል ለማሳየት የሚመርጥ ነው።

ከ 1999 እስከ 2000 ኢትዮጲያ ከኤርትራ ጋር በጦርነት ላይ ነበረች፤ ከዚህ ጊዜ ቀደም ብሎም ሆነ በኋላ ዝቅተኛ ግጭቶችና መተነኳኮሶች ተስተውለዋል። ይህን ለረጅም ጊዜ የቆየውን ግጭት ከልማታዊ መንግሥት ጋር ማገናኘት አይቻልም፤ ነገር ግን ከግብጽ ጋር የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት ማነቆ የሆነው ይኸው የጽንሰ ሐሳቡ መሰረት ከኤርትራም ጋር የነበረውን ግጭት ለመፍታትም ማነቆ ሆኗል። በ2018 ኢትዮጲያ ከጎረቤት ሀገር ኤርትራ ጋር ያደረገችው የሰላም ስምምነት ለሁለት አስርት አመታት የቆየውን ግጭት በማስቆሙ የቀጠናውን መረጋጋት ለማጠናከር ትልቅ ሚና አለው (Okeowo, 2018)።

ሽብርተኝነትን ከመዋጋት አንጻር ኢትዮጲያ የቀጠናው ወሳኝ አጋር ሆና ቆይታለች። ለአብነትም በጅቡቲ የተደረገውን የሽብርተኞች ጥቃት በማጣራትና በተለያዩ ወቅቶች በሶማልያ ያለውን አል-ሻባብ በመዋጋት እገዛ አድርጋለች (US State Department, 2017)። ነገር ግን የኢትዮጲያ ሶማልያውያንን(Hagmann, 2012) እና በአጠቃላይ የሙስሊም ማሕበረሰቡ ተጨቁነዋል(Fasil, 2015)። ኢትዮጲያ በሶማልያ እና በደቡብ ሱዳን በተላኩት የአፍሪካ ሕብረት ሰላም የማስከበር ተልዕኮዎች መሳተፏ ተባባሪ የቀጠና ከባቢን ለማረጋገጥ ያደረገቻቸውን ተግባራት ያሳያሉ። እነዚህ ወታደራዊ እርምጃዎች አውራው/ገዢው ፓርቲ ኃይልን በመጠቀም ያምነበትን ለማሳካት ካለው አስተሳሰብ ጋር ይስማማሉ።

ድብቅ የገንዘብ ዝውውርና ሙስና ለኢትዮጲያ ተግዳሮት ሲሆኑ እነዚህ ችግሮች በልማታዊ መንግሥታት ብቻ የሚታዩ ባሕሪያት አይደሉም። በአፍሪካ ሕብረት በተዘጋጀውና በቀድሞው የደቡብ አፍሪካ ርዕሰ-ብሔር ታቦ ምቤኪ በተመራ መድረክ ላይ ኢትዮጲያ በድብቅ የገንዘብ ዝውውር ከአፍሪካ ሁለተኛ መሆኗ ተዘግቧል (Fekade, 2015)። ከ1970 እስከ 2008 ኢትዮጲያ በግምት ወደ 16.5ቢሊዮን ዶላር (Fekade, 2015) ስታጣ ይህም ያመለጠውን ከፍተኛ እድል አመላካች ነው። ሙስናም በኢኮኖሚው ላይ ከፍተኛ የሆነ ጫናን አሳድሯል። Transparency International (2014) ኢትዮጲያ በ‘‘ከፍተኛ ደረጃጉቦ የተንሰራፋበት’’ ሀገር መሆኗን ይገልጻል። በ2017 ኢትዮጲያ በሙስና ጠቋሚ መለኪያ መሰረት ከ 180 ሀገራት 107 ላይ ነበረች(Transparency International, 2014)። እነዚህ ችግሮች እንዳሉ ቢታወቅም የልማታዊው መንግሥት የጽንሰ ሐሳብ አቋም በራሱ ችግሮቹን ለመፍታት አጋዥ ሆኖ አናገኘውም። ጽንሰ ሐሳቡን በመመልከት ድብቅ የገንዘብ ዝውውር እና ሙስና ላይ ጠንካራና አፋጣኝ ተግባራት እንደሚደረግ ቢገመትም፣ በጠንካራ ቁጥጥርና በገደብ የተሞላው የፋይናንስ ዘርፍ ግልጽ የሆነ የገንዘብ ዝውውር እንዲኖር አላደረገም። በመሆኑም በዚህ አቅጣጫ ምቹ አማራጮችን ሊያቀርብ አልቻለም።

## 4. መደምደሚያ

> ‘‘በገጠር ያለው ድህነት በመንግሥት ብቻ መፍትሔ ሊያገኝ አይችልም፤ ነገር ግን ራሱ ድሃው ቀጥተኛ ተሳታፊ መሆን አለበት። የሰው ሐብት ልማትን በተለይም ድሃውን ለማሳደግ በተናጠል ወይም በጋራ መሰራት ያለባቸው ሥራዎች አሉ፤ ለምሳሌ:- የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ፣ ድሃውን ያሳተፈ የንብረት ባለቤትነት መብት፣ እና የድሃውን ማሕበረሰብ አካታች የሆኑ የሕዝብ ማሕበራትን ማደራጀት’’። (Rahmato, 2008, pp. 276–277)

ልማታዊው መንግሥት የተቋማትን መሰረት በመጣል፣ ሀገራዊ መረጋጋትን በመፍጠር፣ የመሰረተ ልማት አውታሮችን በመገንባትና ተፈላጊውን አቅም በማጎልበት ስኬታማ ሆኗል። ነገር ግን ሀገርን በዘላቂነት ለመገንባት የሚያስፈልጉት የመሰረት ድንጋዮች ማለትም ሚዛናዊ የሥልጣን መዋቅሮች፣ አሳታፊ የኢኮኖሚ ልማት፣ ግጭትን የመፍቻ መንገዶች፣ እና በትብብር ላይ የተመሰረተ የቀጠና ከባቢ የሚፈጥሩ ስኬታማና ሕጋዊ ተቋማት በልማታዊ መንግሥት ጽንሰ ሐሳብ ሊፈጠሩ አይችሉም። ልማታዊ መንግሥት እዝ ተኮር በሆነ መንገድ ቴክኒካዊ መፍትሔ ለሀገሪቱ ለመፈለግ ከዚህ በላይ ስኬት ማምጣት እንደማይችል እናምናለን፤ በተለይም በዚህ ጽንሰ ሐሳብ መሰረት ሐብትን በጥቅም ላይ በማዋል ስኬታማና ተዓማኒ ተቋማትን መገንባት አይቻልም።

ሚዛናዊ የሥልጣን መዋቅሮች ለመመስረት የፖለቲካ ልሂቅ ደምጽ ብቻ ከመስማት በተጨማሪ የሌሎችንም አካላት ድምጽ ለማስተናገድ፣ ዋጋ ለመስጠትና፣ አመኔታ ለመጣል ፈቃደኛ መሆንን ይጠይቃል። ይህም የተቃዋሚ አስተሳሰቦችን ጨምሮ ለሁሉም እድልን የሚፈጥሩ የሕግ፣ የፖሊሲና የሥራ ሂደቶችን ማዘጋጀት ይፈልጋል። ‘የሀገሪቱን ሕዝብ የሚጠብቀውና ለእሱም የሚበጀውን የሚያስብለት ግንባር ቀደሙ ልሂቅ ነው’ የሚለው ትርክት አካታችና አሳታፊ ከሆኑ ሂደቶች ተቃራኒ እሳቤ ያለው ነው። እንዲህ አይነት የአስተሳሰብ መሰረት በጎረቤት ካሉት የዓለም አቀፍ ማሕበረሰብም ጋር ሆነ በሀገር ውስጥ ካሉት ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር መቻቻል እንዳይኖር አድርጓል። የዚህም ውጤት ልማታዊው መንግሥት ምንም እንኳ በመሰረተ-ልማት ግንባታ  ቢሳካለትም ስኬታማና ተዓማኒ እንዳይሆን ግን አድርጎታል። በማክሮ ኢኮኖሚው ላይ ትኩረት ያደረገው የልማት አካሄድ ከአሳታፊ የኢኮኖሚ ልማት ጋር አብሮ መሄድ ይገባዋል። ይህንንም ለማረጋገጥ የመንግሥት የአስተዳደር ሥርዓትን ጠንካራ የሚያደርጉ ብቁ እና ስኬታማ ተቋማትን መፍጠር ያስፈልጋል፤ እንዲህ አይነት ተቋማትም በሀገር ውስጥም ሆነ በሰፊው የቀጠናው ከባቢ አግባብ ያላቸውን የግጭት መፍቻ መንገዶች ለማዘጋጀት አቅምና አመኔታ ይኖራቸዋል።

አመኔታና ሕጋዊነት የሚረጋገጠው ለአለመግባባቶች ምክንያት የሆኑትን ገዳዮች መልክ በማስያዝ ነው፤ ሥር የሰደደውን መበላለጥ መቀነስ የእነዚህ አለመግባባቶች ዋናውና መለወጥ የሚቻለው የችግሩ መንስዔ ነው (በእርግጥ እንደ አካባቢ ንብረት ለውጥ፣ የግብርና የሥነ-ምሕዳር ለውጥ እና አለማቀፍ ገበያም የችግር መንስዔዎች ቢሆኑም እነዚህ በመንግሥት ቀጥታ ቁጥጥር ሥር አይደሉም)። ሥር የሰደደው መበላለጥ እና ፈላጭ ቆራጭ የሆነው የአስተዳደር ሥርዓት ሊለወጡ ካልቻሉ የእድገት ማነቆዎች መሆናቸውን አያቆሙም። በዚህም ጥናት  እንደተመለከትነው ሥር የሰደደው ያልተመጣጠነ እድገትና የመንግሥቱ የአስተዳደር መንገድ የተቆራኙ ናቸው (ይህንን ስንል የመበላለጡ ብቸኛው ምክንያት መንግሥት አንዳልሆነ ግልጽ ሊሆን ይገባል)።

በ2017 ሁኔታዎች ተስፈ የሚሰጡ አልነበሩም። ግጭቶች በሁሉም ቦታ ተዛምተው ሀገር አቀፍ የሆነና የከፋ ችግር የሚፈጥር ይመስል ነበር። በሀገሪቱ ውስጥ የሚስተዋለውን የኢፍትሀዊ  የሀብት ክፍፍል መንስዔዎች ለመቅረፍ እና ሁሉንም አሳታፊ የሆነ የመንግሥት አስተዳደር ሥርዓትን ለመፍጠር ስኬታማና ፈጣን ተግባራትን መሥራት እንደሚያስፈልግ ይህ ጥናት ይሞግታል፤ ይህንንም ማድረግ ከተቻለ አሳታፊ ልማትን ማረጋገጥ ይቻላል። በአዲሱ የመንግሥት አመራር እየተሰሩ ያሉት ማሻሻያዎች ለውጥ ጠቋሚ ናቸው፤ ከቀደመውና በመለስ ከተረቀቀው የልማታዊ መንግሥት እሳቤም ተቃራኒ ይመስላሉ።

ኢትዮጲያ የአሳታፊ የመንግሥት አስተዳደር ሥርዓት ታሪክ ባይኖራትም እንዲህ አይነት ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል ከታንዛንያ መመልከት እንችላለን (Dashwood & Pratt, 1999) (ምንም እንኳን በቅርቡ በታንዛንያ የምንመለከታቸው ሂደቶች ይህ ለውጥ ዘላቂ ሊሆን እንደማይችል ጠቋሚ ቢሆኑም)። የመንግሥት አስተዳደር ሥርዓት ለውጥ ግቡ የመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲን ማስፈን ብቻ ላይሆን ይችላል፤ ነገር ግን ወሳኝ የሆነ የፖለቲካዊና የጽንሰ ሐሳብ ለውጥን ማምጣት ግን ይፈልጋል። ኢትዮጲያኖችም እድሉ ከተሰጣቸው ለመሳተፍ፣ ለመተባበርና መፍትሔ ለመፈለግ ከፍተኛ ተነሳሽነት እንዳላቸው እናምናለን። ዜጎች መፍትሔ ለመፈለግ እድል ሲሰጣቸው የሚያሳዩትንም ተነሳሽነት ለማመሳከር በርካታ ምሳሌዎችን ማንሳት ይቻላል። የኢትዮጲያ ሴት ሕግ ባለሙያዎች ማሕበር በቤተሰብ ሕጉ፣ በወንጀል ሕጉ እና በብሔር ብሔረሰቦች ሕጉ ላይ የነበሩትን አግላይ እና ኢፍትሐዊ አንቀጾች ለማስቀየር የቻሉበት አጋጣሚ ለአብነት ማንሳት ይቻላል (Cochrane & Betel, 2018)። አብዛኛዎቹ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ወደ ሀገር ውስጥ መመለስ መጀመራቸውን ስንመለከት በኢትዮጲያ ለመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲ ማበብ ተስፋ ሰጪ ሁኔታ ይመስላል።

ሥር-ነቀል የሆነ የመንግሥት አስተዳደር ለውጥ ቀላል አይደለም። የሥልጣን ተዋረዶችና የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች ጥያቄ ውስጥ ስለሚገቡ በዚህ ልክ የሆኑ ለውጦች እጅግ ከባድ ናቸው። በመንግሥትና በሕዝቡ መካከል ያለው ቅራኔ በከፍተኛ ሁኔታ እተየካረረ መምጣቱ የለውጡን አስፈላጊነት ግልጽ አድርጎታል። በዚህም ምክንያት የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ሐይለማርያም ደሳለኝ ስልጣኑን በመልቀቅ ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አሕመድ በቦታው ተተክቷል። አዲሱም አስተዳደር ፍትሐዊና ዴሞክራሲያዊ ምርጫን ማድረግን ጨምሮ ሰፊና ሁሉን አቀፍ የሆኑ ማሻሻያዎችን ለማድረግ ያለውን ተነሳሽነት አረጋግጧል (Giorgis, 2018)። ኢትዮጲያ ይበልጡን አሳታፊና የራሷ የሆነ የመንግሥት አስተዳደር መንገድ እንደምትከተል ተስፋ እናደርጋለን። ዜጎችን ለማሳተፍ አዳዲስ አካሄዶችንና እድሎችን ከመፍጠር ጎን ለጎን መንግሥትም የበለጠ ምላሽ ሰጪና አሳታፊ በመሆን ከበፊቱ የተለየ አዲስ ጎዳና መጓዝ ይችላል። ነገር ግን ፖለቲካዊ ለውጥ እንዲመጣ ይህ አካሄድ ብቸኛው አይደለም። በተጨማሪም የኢትዮጲያ ታሪክን መለስ ብለን ስንመለከት እንዲህ አይነቱ ጎዳና ለመተግበር ከባዱ ነው። ሆኖም ይህችን አይነት ሀገር መመስረት የሁሉም ኢትዮጲያዊ ፍላጎት እንደሆነ በየቦታው እየተመለከትን ነው። አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትርም እያበረታታ ያለው እንዲህ አይነት ተስፋ ያላትን ኢትዮጲያ ነው፤ የልማታዊ መንግሥት አክትሞ ዴሞክራሲያዊ ልማት የሚያብባትን።

## ዋቢ ሀትመቶች


Abbink, J. (2003a). Badme and the Ethio-Eritrean border: The challenge of demarcation in the post-war period. *Africa, 58*(2), 219–231. Retrieved from https://www.jstor.org/stable/40761693?seq=1#page_scan_tab_contents

Abbink, J. (2003b). Ethiopia–Eritrea: Proxy wars and prospects of peace in the Horn of Africa. *Journal of Contemporary African Studies, 21*, 407–425. https://doi.org/10.1080/0258900032000142446

Abbink, J. (2011). Ethnic-based federalism and ethnicity in Ethiopia: Reassessing the experiment after 20 years. *Journal of Eastern African Studies, 5*, 596–618. https://doi.org/10.1080/17531055.2011.642516

Abbink, J. (2017). *A decade of Ethiopia: Politics, economy and society 2004-2016*. Leiden: Brill.

Abebe, S. G. (2014). *The last post-Cold War Socialist Federation: Ethnicity, ideology and democracy in Ethiopia*. Farnham: Ashgate.

Abraham, K. (1994). *Ethiopia – From bullets to the ballot box: The bumpy road to democracy and the political economy of transition*. Lawrenceville, NJ: Red Sea Press.

Amnesty International. (2012). *Ethiopia: The 2009 Charities and Societies Proclamation as a serious obstacle to the promotion and protection of human rights in Ethiopia*. Amnesty International's written statement to the 20th Session of the UN Human Rights Council (18 June–6 July). Retrieved from the Amnesty International website: https://www.amnesty.org/download/Documents/16000/afr250072012en.pdf

Ang, Y. Y. (2016). *How China escaped the poverty trap*. Ithaca, NY: Cornell University Press.

Ayele, B. (2018). Council Arise to Reform Anti-Terrorism, Media Law. Retrieved from the AllAfrica website: https://allafrica.com/stories/201807030771.html

BBC News. (2016, August 22). What is behind Ethiopia's wave of protests? Retrieved from https://www.bbc.com/news/world-africa-36940906

Berhane, G., Gilligan, D. O., Hoddinott, J., Kumar, N., & Taffesse, A. S. (2014). Can social protection work in Africa? The impact of Ethiopia's productive safety net programme. *Economic Development and Cultural Change, 63*, 1–26. https://doi.org/10.1086/677753

Bluffstone, R., Yesuf, M., Bushie, B., & Damite, D. (2008). *Rural livelihoods, poverty, and the Millennium Development Goals: Evidence from Ethiopian survey data* (EfD Discussion Paper No. 08). Retrieved from the Environment for Development website: http://www.efdinitiative.org/publications/rural-livelihoods-povertyand-millennium-development-goals-evidence-ethiopian-survey

Booth, D. (2012). *Development as a collective action problem: Addressing the real challenges of African governance*. Retrieved from the Overseas Development Institute website: https://www.odi.org/publications/6869-synthesis-report-development-collective-action-problem-adressing-real-challenges-african-governance

Bouh, A. M., & Mammo, Y. (2008). Indigenous conflict resolution mechanisms on range lands in Somali Regional State, Ethiopia. *Nomadic Peoples, 12*(1), 109–121. https://www.jstor.org/stable/43123815

Brown, T., & Teshome, A. (2007). *Implementing policies for chronic poverty in Ethiopia*. Retrieved from the Chronic Poverty Research Centre website: http://www.chronicpoverty.org/uploads/publication_files/CPR2_Background_Papers_Brown-Teshome.pdf

Cafer, A. M., Willis, M. S., Shimelis, B., & Mamo, M. (2015). Growing healthy families: Household production, food security, and well-being in South Wollo, Ethiopia. *Culture, Agriculture, Food and Environment, 37*(2), 63–73. https://doi.org/10.1111/cuag.12053

Carothers, T., & de Gramont, D. (2013). *Development aid confronts politics: The almost revolution*. Washington, DC: Carnegie Endowment for International Peace.

Clapham, C. (2018). The Ethiopian developmental state. *Third World Quarterly, 39*, 1151–1165 https://doi.org/10.1080/01436597.2017.1328982

Cliffe, L., Love, R., & Tronvoll, K. (2009). Conflict and peace in the Horn of Africa. *Review of African Political Economy, 36*(120), 151–163. https://doi.org/10.1080/03056240903086485

Cochrane, L. (2017). *Strengthening food security in rural Ethiopia* (Doctoral dissertation). The University of British Columbia.

Cochrane, L., & Tamiru, Y. (2016). Ethiopia's productive safety net program: Power, politics and practice. *Journal of International Development, 28*, 649–665. https://doi.org/10.1002/jid.3234

Cochrane, L., & Bekele, Y. W. (2018). Contextualizing narratives of economic growth and navigating problematic data: Economic trends in Ethiopia (1999–2017). *Economies, 6*(4), 64. https://doi.org/10.3390/economies6040064

Cochrane, L., & Betel, B. B. (2018). Pathways of legal advocacy for change: Ethiopian Women Lawyers Association. *Forum for Development Studies*. https://doi.org/10.1080/08039410.2018.1534752

Cochrane, L., & Rao, N. (2019). Is the push for gender sensitive research advancing the SDG agenda of leaving no one behind? *Forum for Development Studies, 46*, 45–65. https://doi.org/10.1080/08039410.2018.1427623

Dashwood, H. S., & Pratt, C. (1999). Leadership, participation, and conflict management: Zimbabwe and Tanzania. In T. M. Ali & R. O. Matthews (Eds.), *Civil wars in Africa: Roots and resolution* (pp. 223–254). Montreal & Kingston: McGill-Queen's University Press.

de Waal, A. (2012). The theory and practice of Meles Zenawi. *African Affairs, 112*(446), 148–155. https://doi.org/10.1093/afraf/ads081

de Waal, A. (2015). *The real politics of the Horn of Africa: Money, war and the business of power*. Cambridge: Polity Press.

DFID. (2016). *Building stability framework*. Retrieved from the Department for International Development website: https://assets.publishing.service.gov.uk/media/5968990ded915d0baf00019e/UK-Aid-Connect-Stability-Framework.pdf

DHS. (2006). *Ethiopia: Demographic and health survey 2005*. Retrieved from the Demographic and Health Surveys Program website: https://www.dhsprogram.com/pubs/pdf/fr179/fr179%5B23june2011%5D.pdf

ENA. (2018, July 6). Allocating huge budget for pro-poor program creates opportunity to sustain economy: PM. Ethiopian News Agency. Retrieved from the https://www.ena.et/en/2018/07/06/allocating-huge-budget-for-pro-poor-program-creates-opportunity-to-sustain-economy-pm/

Evans, P., & Rauch, J. E. (1999). Bureaucracy and growth: A cross-national analysis of the effects of 'Weberian' state structures on economic growth. *American Sociological Review, 64*, 748–765. https://www.jstor.org/stable/2657374

Fantini, E. (2013). *Developmental state, economic transformation and social diversification in Ethiopia* (ISPI Analysis No. 163). Retrieved from the Istituto per gli Studi di Politica Internazionale website: https://www.ispionline.it/it/pubblicazione/developmental-state-economic-transformation-and-social-diversification-ethiopia-7650

FAO. (2014). *Qualitative research and analyses of the economic impacts of cash transfer programmes in sub-Saharan Africa: Ethiopia country case study report*. Retrieved from the Food and Agriculture Organization website: http://www.fao.org/3/a-i4276e.pdf

Fasil, M. (2015, August 3). An Ethiopian court jailed Muslim leaders, activists to lengthy terms. *Addis Standard.* Retrieved from http://addisstandard.com/an-ethiopian-court-jailed-muslim-leaders-activists-to-lengthy-terms/

Fekade, B. (2015, February 15). Ethiopia: Panel names one of Ethiopia top sources for illicit financial flow. *The Reporter*. Retrieved from the AllAfrica website: https://allafrica.com/stories/201502090215.html

Freedom House. (2018). *Freedom in the world: Ethiopia profile*. Retrieved from the Freedom House website: https://freedomhouse.org/report/freedom-world/2018/ethiopia

Gebremariam, F. M. & Bayu, A. M. (2017). Ethiopia: A Democratic Developmental State? ILIRIA International Review, 7, 153-170.

Gill, P. (2010). *Famine and foreigners: Ethiopia since Live Aid*. Oxford: Oxford University Press.

Giorgis, H. (2018). Abiy Ahmed Meets the Ethiopian Diaspora. The Atlantic. Retrieved from https://www.theatlantic.com/entertainment/archive/2018/08/abiy-ahmed-meets-the-ethiopian-diaspora/566591/

Government Communication Affairs Office. (2018, July). PM Abiy Ahmed's first 100 days. Retrieved from http://www.gcao.gov.et/web/en/-/pm-abiy-ahmed-s-first-100-days

Hagmann, T. (2012, July 11). Supporting stability, abetting repression. *The New York Times.* Retrieved from https://www.nytimes.com/2012/07/12/opinion/abetting-repression-in-ethiopia.html

Human Rights Watch. (2015). *'Journalism is not a crime': Violations of media freedom in Ethiopia*. Retrieved from the Human Rights Watch website: https://www.hrw.org/report/2015/01/21/journalism-not-crime/violations-media-freedoms-ethiopia#

Husmann, C. (2016). Marginality as a root cause of poverty: Identifying marginality hotspots in Ethiopia. *World Development, 78*, 420–435. https://doi.org/10.1016/j.worlddev.2015.10.024

Kestler-D'Amours, J. (2018, February 20). Ethiopia: Mass protests 'rooted in country's history'. *Aljazeera*. Retrieved from https://www.aljazeera.com/news/2018/02/ethiopia-mass-protests-rooted-country-history-180219130441837.html

Khan, M. H. (2007). *Governance, economic growth and development since the 1960s* (DESA Working Paper No. 54). Retrieved from https://www.un.org/development/desa/publications/working-paper/governance-economic-growth-and-development-since-the-1960s

Lefort, R. (2013). The theory and practice of Meles Zenawi: A response to Alex de Waal. *African Affairs, 112*(448), 460–470. https://doi.org/10.1093/afraf/adt021

Lie, J. H. S. (2010). *Supporting the Nile Basin Initiative: A political analysis 'beyond the river'* (Desk review study commissioned by NORAD). Retrieved from https://www.academia.edu/2243972/Supporting_the_Nile_Basin_Initiative_A_Political_Analysis_Beyond_the_River

Mohammed, O. (2018, August 4). Eritrean Airlines starts regular flights to Addis, improving relations: Minister. *Reuters*. Retrieved from https://www.reuters.com/article/us-ethiopia-eritrea-airlines/eritrean-airlines-starts-regular-flights-to-addis-improving-relations-minister-idUSKBN1KP0CX?il=0

Naqvi, N. (2018). Finance and Industrial Policy in Unsuccessful Developmental States: The Case of Pakistan. Development and Change, 49, 1064-1092. https://doi.org/10.1111/dech.12424

NPC. (2015). *MDG report 2014 – Ethiopia*. Addis Ababa: National Planning Commission.

NPC. (2016). *Growth and transformation plan (GTP) of the Federal Democratic Republic of Ethiopia (2015/16–2019/20)*. Addis Ababa: National Planning Commission.

NPC. (2017). *The 2017 voluntary national reviews on SDGs of Ethiopia: Government commitments, national ownership and performance trends*. Addis Ababa: National Planning Commission.

Oakland Institute. (2013). *Development aid to Ethiopia: Overlooking violence, marginalization, and political repression*. Retrieved from the Oakland Institute website: https://www.oaklandinstitute.org/development-aid-ethiopia

OPHI. (2017). *OPHI country briefing 2017: Ethiopia*. Oxford Poverty and Human Development Initiative. Oxford: University of Oxford.

Okeowo, A. (2018, August 2). Will the leaders of Eritrea and Ethiopia finally deliver peace to their people? *The New Yorker*. Retrieved from https://www.newyorker.com/news/news-desk/will-the-leaders-of-eritrea-and-ethiopia-finally-deliver-peace-to-their-people

Pankhurst, R. (1966). *State and land in Ethiopian history*. Addis Ababa: Institute of Ethiopian Studies.

Planel, S. (2014). A view of a *bureaucratic* developmental state: Local governance and agricultural extension in rural Ethiopia. *Journal of Eastern African Studies, 8*, 420–437. https://doi.org/10.1080/17531055.2014.922745

Rahmato, D. (2008). *The peasant and the state: Studies in agrarian change in Ethiopia, 1950s-2000s*. Addis Ababa: Custom Books.

ReliefWeb. (2018). Ethiopia: Drought 2015-2018 [Web page]. Retrieved from the ReliefWeb website: https://reliefweb.int/disaster/dr-2015-000109-eth

Reuters. (2018, July 19). Tearful reunions as Ethiopia-Eritrea flights resume. Retrieved from the Reuters website: https://www.reuters.com/news/picture/tearful-reunions-as-ethiopia-eritrea-fli-idUSRTX6BY6O

Routely, L. (2012). Developmental states: a review of the literature. *ESID Working Paper No. 03*. ISBN: 978-1-908749-07-9

Sisay A. Y. (2012). CSO law in Ethiopia: Considering its constraints and consequences. *Journal of Civil Society, 8*, 369–384. https://doi.org/10.1080/17448689.2012.744233

*The Economist.* (2018, July 10). An unexpected embrace: Ethiopia and Eritrea put an end to two decades of conflict. Retrieved from https://www.economist.com/middle-east-and-africa/2018/07/10/ethiopia-and-eritrea-put-an-end-to-two-decades-of-conflict

*Transparency International*. (2014, October 6). Transparency International data shows Ethiopia suffers from high levels of bribery. Retrieved from the Transparency International website: https://www.transparency.org/news/pressrelease/transparency_international_data_shows_ethiopia_suffers_from_high_levels_of

UN. (2011). *World population prospects: The 2010 revision*. Retrieved from the United Nations website: http://www.un.org/en/development/desa/publications/world-population-prospects-the-2010-revision.html

UN. (2015). *World population prospects: The 2015 revision*. Retrieved from the United Nations website: http://www.un.org/en/development/desa/publications/world-population-prospects-2015-revision.html

UNDP. (2015). *Human development report 2015: Work for human development*. Retrieved from the United Nations Development Programme website: http://hdr.undp.org/en/content/human-development-report-2015-work-human-development

UNDP. (2017). *Ethiopia: Human development indicators*. Retrieved from the United Nations Development Programme website: http://hdr.undp.org/en/countries/profiles/ETH#

US State Department. (2017). *Country reports on terrorism 2016*. Retrieved from the United States Department of State website: https://www.state.gov/j/ct/rls/crt/2016/

Vaughan, S. (2011). Revolutionary democratic state-building: Party, state and people in the EPRDF's Ethiopia. *Journal of Eastern African Studies, 5*, 619–640. https://doi.org/10.1080/17531055.2011.642520

Whittington, D., Waterbury, J., & Jeuland, M. (2014). The Grand Renaissance Dam and prospects for cooperation on the Eastern Nile. *Water Policy, 16*, 595–608. https://doi.org/10.2166/wp.2014.011b

Woldegiyorgis, A. (2014). The Ethiopian developmental state and its challenges. Retrieved from https://doi.org/10.2139/ssrn.2512907

World Bank. (2017). *Ethiopia* [Data set]. Retrieved from World Bank website: http://data.worldbank.org/country/ethiopia

World Bank. (2018). *Doing business 2018: Reforming to create jobs—Ethiopia*. Retrieved from http://documents.worldbank.org/curated/en/824081509690919602/Doing-Business-2018-reforming-to-create-jobs-Ethiopia

Zenawi, M. (n.d.). *African development: Dead ends and new beginnings*. Preliminary draft. Retrieved from http://www.meleszenawi.com/african-development-dead-ends-and-new-biginnings-by-meles-zenawi/

Zenawi, M. (2012). States and markets: Neoliberal limitations and the case for a developmental state. In A. Noman, K. Botchwey, H. Stein, & J. E. Stiglitz (Eds.), *Good growth and governance in Africa: Rethinking development strategies* (pp. 140–174). Oxford: Oxford University Press.

Zewde, B. (2014). *The quest for socialist utopia: The Ethiopian student movement c. 1960-1974*. Addis Ababa: Addis Ababa University Press.